### 2.2.2. በሐዋርያት ከተሰበከው የተለየ ወንጌል የሚሰብክ ...

ለመንፈሳዊው ትምህርት መስፋፋት ትልቅ ድርሻ ያላቸውና ምዕመናን በቃለ እግዚአብሔር ታንጸው እንዲያድጉ በመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ ትርጓሜ ላይ ተመሥርተው የሚዘጋጁ መንፈሳዊ መጻሕፍት ጠቃሚዎች ናቸው። ሆኖም ግን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆኑ ማንኛቸውንም መንፈሳዊ መጻሕፍት የእምነት መመሪያ ለማድረግ ከመጣር በፊት በቃለ እግዚአብሔር መመርመራቸው ወሳኝ ነው።

ስለዚህም እንደ ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ዮሐንስ አራተኛው ለሃይማኖት ትምህርት በቃለ እግዚአብሔር ላይ ያልተመሠተና የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉባኤም በቃለ እግዚአብሔር ፈትሸው ያላወጡት መጽሐፍ የተፋለሰ ሐሳብን እስካንጸባረቀ ድረስ በልዩ ወንጌልነት ሊወገዝ ይገባዋል። ስለ ልዩ ወንጌል ስናስብ የግዴታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማያጣቅስን ለትክክለኛነት መሥፈርት አድርጎ ማስቀመጥ አይገባንም። እንዲያውም እጅግ የከፋው መጽሐፍ ቅዱስን ከአውዱ ውጪ እየጠቀሰ የእግዚአብሔርን እውነት ከማጣመም የሚመነጭ መናፍቅነት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ሲጽፍላቸው፦ «...እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፤ የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ። ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን።» ይላል (ገላ.1:7-8)። እንግዲህ በሐዋርያት ከተሰበከው የእግዚአብሔር እውነት ውጪ የሆኑና በቅዱሰነት ስም ተገሰጠልኝ እያሉ የሚጻፉ መጻሕፍት ከመሐመዳውያን



ያልተለየ ተግዳሮትን በወንጌል ላይ ማምጣታቸውን ታሪክ ያመለክተናል።

ስለዚህም የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን በቃለ እግዚአብሔር እውነት አርነት ለመውጣት በእግዚአብሔር እውነት ላይ ከፈጸመችው ከእንዲህ ዓይነቱ በደል በንስሐ ወደ አምላኳ እንድትመለስና መሠረታዊውም የእምነት ትምህርት የሚያፋልሱ መጻሕፍትን በመመርመር ከሃይማኖት ትምህርቷ ውጭ መሆናቸውን ማጋለጧ ወቅታዊነት ያለው የተሃድሶ ጥያቄ ምላሽ ነው።

### 2.2.3. እንማማር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በዓለም ካሉ አብያተ ክርስቲያናት በተለየ መንገድ ሰፊ ቀኖና ያላት ከመሆኗ በተጨማሪ በርካታ የሥርዓትና የአገልግሎት መጻሕፍትም አሏት። ይህ ደግሞ በዘመን ርዝመት መጻሕፍትን ሁሉ በእኩል እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያሰባቸው አድርጎ መቁጥርን አስከትሏል። ከዚህም የተነሣ እጅግ በጣም መሠረታዊ በሆኑ የሃይማኖት ትምህርቶችም ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጦች ሊንጸባረቁ ይስተዋላል። ስለዚህም እነዚህ መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ገዢ እንዳይሆኑ ቦታቸውን ሊይዙ ይገባል።

ጉዳዩ አስቀድሞ የቤተክርስቲያኒቱን ሊቃውንት ያስቆጣ ነው። ቤተክርስቲያኒቱ ኦፊሲየላዊ በሆነ መንገድ ከቀኖና እና ከዳግማዊ የቀኖና መጻሕፍት ላይ እንደተመሠረቱና በአበው እንደተደረሱ የምታምንባቸውን መጻሕፍት ለብሉይና ለሐዲስ ምሥጢራት ማብራሪያነት

እንደምትገለገልባቸው ማስፈሯ መልካም ቢሆንም በአተገባበር ረገድ የሀገራችን ችግር በሆነው የአፈጻጸም ተግዳሮት ለሰባ ሆናለች።

ለዚህም ደግሞ በምሳሌነት የምጠቅሰው በ1970ዎቹ የሊቃውንት ጉባዔው በተዓምረ ማርያም ላይ በደረሰበት የጥናት ውጤት መጽሐፉ ልብ ወለድ እንደሆነ ለሕዝብ ባሰራጨው መጽሐፍ የመግለጡን ዓይነት ድርጊት ለአብነት ያህል መጥቀስ ይቻላል። ሆኖም ግን ለዘመናት በዚህ የስህተት አካሄድ የተጠቁና ባልተረዱት የሃይማኖት ቅናት ውስጥ የወደቁ ምዕመናንን ተቃውሞ ፍራቻ መጻሕፍቱ ከሚሸጡባቸው ሱቆች መሰቀማቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው።

እንግዲህ ሊቃውንቱ ባመኑበት አካሄድ እንኳ የተባሉና ዕድሜ የጠገቡ አያሌ መጻሕፍት በኢትዮጵያ የብዙዎች ደም ያለባቸው በመሆናቸው በዚሁ ምግባራቸው ይዘከሩ ዘንድ ለታሪክ ቅርስነት ከመዋል ውጪ ለሃይማኖት ትምህርት ስለማይሆኑን በፍርድም ቀን መጽናት ቢችሉ ኤግዚቢት ይሆኑ ዘንድ ወደ መቆያቸው ሙዝየም መግባት ይኖርባቸዋል። እነዚህ ለዘመናት በቅዱሳት መጻሕፍት ሳይመረመሩና ለሐዲስም ሆነ ለብሉይ ማብራሪያነት የሌላቸው መጻሕፍት በሕዝቡ ልቡና ያደረሱትን ተጽእኖ ለመሻርና መጪውን ትውልድ እንኳን ለመታደግ ሥራቸው መነቀል ይኖርበታል።

ይህንን ያልኩበት አብይ ምክንያት የቤተክርስቲያኒቱ ሊቃውንት የሚያፍሩባቸውና ስማቸውን ለመግለጥ ያልወደዷቸው ከቃለ እግዚአብሔር ውጪ በሆኑ የእሮጊቶች ተረት የተሞሉ፣ ለብሉይና ለሐዲስ ማብራሪያ መሆን ይቅርና በተቃራኒ አቅጣጫ ከቆናና መጻሕፍት በላይ የሥልጣን ምንጭ ሆነው ቤተክርስቲያኒቱን



የሚነዱአት አያሌ በገድል ስም የተተረኩ መጻሕፍት ስላሉአት ነው። ስታሪክ ሂደት በአንድ ወቅት እንደ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ካሉ ነገሥታት ጋር ያበሩ አባቶች ያስፋፉት ከሃይማኖት ትምህርት ያፈነገጠ ኑፋቄ ይታረም የሚሉትን ሁሉ ከመንገድ እያስወገዱ የቤተክርስቲያኒቱን እውነተኛ ገጽታ ለማጥፋት በመብቃታቸው ነው።

III. ከታሪካዊ ሥነ መለኮት የምንማማረው

3.1. መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት በተዋሕዶ ግንዛቤ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መሠረተ እምነትዋን የምትገልጥባቸው አምስት ዋና ዋና ነጥቦች አሉዋት። እነዚህ አምስቱ ነጥቦች የሚያተኩሩት እጅግ መሠረታዊ በሆኑ አስተምህሮቶች ላይ ነው። በቤተክርስቲያኒቱ አተረጓጎም መሠረት ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 14:19 "ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ *አምስት ቃላት* በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ።" ያለው ስለ አምስቱ አዕማድ (መሠረታዊና ምእመናንን በትምህርተ ሃይማኖት ለማጽናት ጠቃሚ የሆኑ አስተምህሮዎች) እንደሆነ ይናገራሉ። እነዚህ አምስቱ አዕማደ ምሥጢራት በፀሎተ ኃይማኖት መዘርዘራቸውን ይገልጻሉ። እነርሱም:- ምሥጢረ ሥላሴ (ትምህርተ እግዚአብሔር)፥ ምስጢረ ሥጋዌ (ነገረ-ክርስቶስ)፥ ምሥጢረ ጥምቀት፥ ምሥጢረ ቁርባን እና ምስጢረ ትንሣኤ ሙታን ናቸው። በእነዚህ መሠረታዊ አስተምህሮዎች ዙሪያ የሚሰነዘሩ ትምህርቶችን በመዳሰስ ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነታ በመቅረብ እና በመማማር አንድ ለመሆን ይቻል ዘንድ መሠረታዊ ትምህርቶችን በመዳሰስ እንጀምር:-

### 3.1.2. ነገረ-ክርስቶስ

#### 3.1.2.1. አምላክ ሰው ሆነ - በተዋሕዶ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በዮሐ 1:14 ላይ ተመሥርታ ከሥላሴ አንዱ አካል አካላዊ ቃል ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ (ወስዶ) አምላክ ሰው፥ ሰውም አምላክ ሆነ ብላ ታምናለች።

ሠይፈ ሥላሴ ይህን የተዋሕዶን ምሥጢር በነፍስና በሥጋ አንድነት ሲገልጹ :- «ወልደ አብ ወልደ ማርያም ስተዋሕዶ ከበረ፥ ቃል ከሥጋ ጋር በተዋሐደ ጊዜ በተዋሕዶው ፍልጠት (መክፈል)፥ ቡአዴ (መነጣጠል) ውላጤ (መጠፋፋት) እና ሚጠት (መለወጥ) የለበትም ስተዋሕዶው እንደ ነፍስና ሥጋ ነው! ሥጋ ግዘፉን ሳይለቅ ነፍስም ርቀትዋን ሳትለቅ ተዋሕደው አንድ ሰው እንዲባል ቃል ርቀቱን ትቶ ሳይገዝፍ ምልዓቱንና ስፋቱንም ትቶ ሳይወሰን ትስብእትም ግዘፉን ለቆ ሳይረቅ ሳይዋጥና ሳይጠፋ ውሱንነቱንም ለቆ ምሉዕና ስፉሕ ሳይሆን ነው።»[66] ብለዋል።

በተጨማሪም የነፍስና የሥጋ አንድነት የየራሳቸውን መለያ ጠባያት (Attributes) ሳይለቁ ሰው እንደሚያሰኙ «ቃል» (Logos) የራሱን መለያ ጠባይ (Attribute) ሳይለቅ ትስብእት (ሰው) ተክለ ሰውነቱን ሳይለቅ

[66] ሠይፈ ሥላሴ፥ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይ. ... ገጽ. 25



ክርስቶስ ሆነ ሥጋ በተዋሕዶ መለኮት የሆነው የራስ የሆኑ ነገሮቹን (properties) ሳይለቅ ነው በማለት ያብራሩታል።[67]

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የአምላክ ሰው ሆኖ ወደ ምድር መምጣት ከተዋሕዶ ፅንሰ ሐሳብ ተነጥሎ መታየት የማይቻል መሆኑ በአካሉ ላይ በአሁኑም ወቅት ምንም ዓይነት ለውጥ እንዳልተከናወነና ያው የትሥጉት (ሥጋ የሆነው) አካል ራሱ እንዳለ በማመን ላይ የተመሠረተ ትምህርት አላት። ሆኖም ግን ከስቅለቱ በፊትና በኋላ በግብር ረገድ ለውጥ እንዳለም ታምናለች። ይህ ደግሞ የማዳን ተልዕኮውን ከማጠናቀቁ የተነሣ ለሰው ልጆች ድነት አስፈላጊ በሆነው በግብረ ትሥብዕት ሳይሆን በአሁኑ ወቅት በአብ ፊት ከብሮ በግብረ መለኮት እንዳለ ባላት እምነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው። (ለተጨማሪ ማብራሪያ «እኔን ማን ትሉኛላችሁ?» የተሰኘውን መጽሐፍ ከገጽ. 108-112 መመልከት ይቻላል። ከዚሁ ፅንሰ ሃሳብ ጋር በተያያዘ ከሚነሡ ሥነ መለኮታዊ ትምህርቶች አንዱ ከምልጃ ትምህርት ጋር የተያያዘ ነው። ይህንንም በሚከተለው ርእስ ሥር በስፋት ለመመልከት እንሞክራለን።

በዚህም ላይ በመመሥረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ ከኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲየናት ጋር በመሆን ከሌሎች የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተክርስቲያናት (የኬልቄዶንን ውሳኔ ከተቀበሉቱ) ጋር ባደረገችው ውይይት የሚከተለውን መግለጫ በቅዱስ ሲኖዶሱ በኩል በተዘጋጀ

[67] ዝኒ ከማሁ

### 3.1.2.2. እንማማር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፅንስ ከወላጆቹ ሥጋና ነፍስ እንደሚነሣ (እንደሚወስድ) ያላት እሳቤ፤ በሥነ ሰብ ፍልስፍና ላይ የተመረኮዘ መሆኑን መረዳት የሚያስችለን፤ ነፍስ ከእናትና ከአባት ትከፈላለች እንጂ አትፈጠርም ከመዝገበ ነፍስም አትላክም የሚለው እምነቷ ፍልስፍናዊ እሳቤ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ነው።[74]

ነፍስ ከመዝገበ ነፍስ የምትላክ ስለመሆኗ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ማቅረብ እንደማይቻል ሁሉ፤ ይህንን ነፍስ ከእናትና ከአባት ትከፈላለች የሚለውን ፍልስፍናዊ እሳቤም በመጽሐፍ ቅዱሳዊም ሆነ በሣይንሳዊ መንገድ ማስረገጥ የሚቻል አይመስለኝም። ዋናው ቁም ነገር ግን የቃል (Logos) ሥጋ መሆን የእምላክ ሰው መስሎ መምጣትን ሳይሆን ሰው ሆኖ መምጣትን በማመልከቱ ላይ ነው።

ታሪካዊ ሥነ መለኮት (Historical Theology) በመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ መለኮት (Biblical Theology) ላይ መመሥረት ይኖርበታል። በሥነ መለኮት አከራካሪ ነጥቦች ላይ በዋናነት በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት ቋንቋ ያለውን ትርጉም ለመረዳት መሞከር አስፈላጊ ነው። በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ክርስቶስን «አማላጅ» እንደሆነ የተተረጎሙ ክፍሎችን ከግሪኩ ቃል አንጻር መመልከት ያሻል።

እስቲ ከመስቀለ ሞቱ በፊት ያሉትን ክፍሎች እንመልከት፡- በሉቃስ 22:32 ላይ «... እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ አማለድሁ፤... »



ይላል። በዚህ ክፍል ላይ አማለድሁ በመባል ከግሪክ ወደ አማርኛ የተመለሰው ቃል εδεηθην (ኤዴቴን) የሚል ሲሆን ምንጩ δεομαι (ዴእማይ) ነው። ትርጉሙም መጠየቅ፥ መለመን፥ ባብዛኛውን ጊዜም «እባክህ! ... » ለሚል የጸሎት ጥያቄ የሚውል ነው። ስለዚህም በዚህ ክፍል ላይ ከመስቀለ ሞቱ በፊት ጌታ ኢየሱስ አብን መለመኑን መገንዘብ ይቻላል። በሉቃስ 23:34 ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳለ፡- «አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ።» ማለቱን በተመለከተ በግሪኩ αφες (አፌስ) ምንጩ αφιημι (አፊሄማይ) ሲሆን ትርጉሙም «ይቅር በል፥ ምሕረትን አድርግ፥ ታገስ (ቻል አድርግ) በማለት ወደ አብ መቅረብን አመላካች ነው።

ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ በተለይ በመልእክታት ውስጥ በሐዋርያው ጳውሎስና በዕብራውያን ጸሐፊ አማካኝነት የተንጸባረቁት ክፍሎች ስንመለከት በግሪኩ ምንጫቸው εντυγχανω (ኤንቱግካንዎ) እና μεσιτης (ሜስቴስ) የሚሉ ቃላትን ተጠቅመዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ 8: 34 ላይ በአማርኛ ቋንቋ፡- «... ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።» ተብሎ የተተረጎመው ክፍል εντυγχανει (ኤንቱግካንይ) የሦስተኛ መደብ ነጠላ ሆኖ ምንጩ εντυγχανω (ኤንግካንዎ) ነው። የዚህ የግሪኩ ቃል ትርጉም፡- በውክልና ወደ እግዚአብሔር መቅረብ፥ አቤቱታ ማቅረብን፥ በፍርድ ቤት በዳኛ ፊት ይግባኝ ማለትን ያመለክታል።

[74] ሠይፈ ሥላሴ፥ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖት ... ገጽ 24

ስለዚህ የግሪኩ ቃል ካሉት የትርጉም አማራጮች ትክክለኛውን ለመያዝ በሚደረግ ጥረት ወሳኙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ ዐውደ ምንባብ ነው:: ሮሜ 8:31-33 እንዲሁም ቁጥር 35 ከተቃውሞ÷ ከክስና ክፍርድ ጋር በአጅጉ የተቆራኘ ነው:: ስለዚህም ካሉት የትርጉም አማራጮች በፍርድ ቤት በዳኛ ፊት ይግባኝ ማቅረብን የሚያመለክተው ትርጉም ዐውዳዊ ነው ማለት ያስችላል:: ይህ ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ማማለድ ተብሎ ለተተረጎመው ቃል ምንጩ በማለዳ ገስግሶ ፍርደኛውን ክፍርድ ለማስመለጥ የሚወሰድ ባህላዊ ፅንሰ ሐሳብ ላይ የተመረኮዘ ሆኖ እኛን ወክሎ በአብ ፊት በመታየት ይግባኝ ማቅረቡን አመላካች እንደሆነ መግለጽ ያስችላል::

ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ አውድ መሠረት ክርስቶስ ለሰው ልጆች በሠራው የአድኅኖት ሥራው በአብ ፊት እንደሚቀርብ አመላካች ነው:: ስዚህም የተነሣ ስማዳን ተልእኮው አንጻር የከፈለው መሥዋዕትነት በእግዚአብሔር አብና በአማኞች መካከል የመግባቱን ድርሻ የሚያሣይ በመሆኑ ከአብ ጋር እኩል እንዳይደለ አመልካች ተደርጎ መቆጠሩ ትክክል አይደለም:: ይልቁንም ለአብ የግብር ቅደም ተከተል (Functional Subordination) ያለው መሆኑን እንደሚያመለክት ማስተዋል ያሻል:: ክዚህም የተነሣ በአንዳንዶች ዘንድም ሥጋና መለኮትን በመነጣጠል በሥጋው ይማልድልናል በመለኮቱ ደግሞ ለልመናችን መልስ ይሰጣል ሲባል የሚደመጠውም ክቅዱስ ቁርሎስም ሆነ ከኬልቄዶን ጉባኤ ውሳኔ ጋር ፈጽሞ የማይጣጣም ክመሆኑም ባሻገር ለመረዳት አስቸጋሪ የሆነን ክፍል ከአመክንዮት ውጪ ለመፍታት መሞከሩ ተገቢ አይደለም::



በጣም የሚገርመውና በቤተክርስቲያን አባቶች ዘንድ ብዙም ትኩረት ያልተቸረው÷ በአወዛጋቢነቱም የማይጠቀሰው በዚሁ በሮሜ 8: 26 እና 27 ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ ግብርም ሲገልጽ ይህንኑ የግሪክ ቃል የሚጠቀም ሲሆን በአማርኛው ትርጉሙም መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት እንደሚማልድልን፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን እንደሚማልድ ይገልጻል:: ይህም ደግሞ የመለኮት መበላለጥን ሳይሆን ስለ እኛ ወደ አብ መቅረቡ የግብር ቅደም ተከተልን (Functional Subordination) አመላካች እንጂ የህላዌ (Ontology) መበላለጥን እንደማያመለክት ማስተዋል ያሻል::

ሌላውና ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞ. 2:5 ላይ «... በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ÷ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው: ...» ይላል:: በግሪኩ μεσιτης (ሜስቴስ) ማለት በሁለት ወገኖች መካከል ያለን ጠብ ለማስወገድ በሽምግልና ጣልቃ መግባት ወይም ስምምነትን ለማውረድ መካከል መግባት ማለት ነው:: ይህም ደግሞ የክርስቶስን የግብር ቅደም ተከተል (Functional Subordination) እንጂ በማንነቱ ከአብ ያነሰ (Ontological Hirarchy) መሆንን ፈጽሞ አያመለክትም::

በዕብራውያን 7:24-25 ላይም:- «... የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና÷ ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል::» ይላል:: በዚህም ክፍል ላይ የግሪኩ ቃል εντυγχανειν (ኤንቱግካንኢይን) εντυγχανω (ኢንቱግካንም) ከሚለው ከስርወ ቃሉ

የተገኘና ሊያማልድ ተብሎ የተተረጎመ ነው:: ክፍሉ ማድረግ የማይችል ለምኖ የሚያስደርግ የሚልን ትርጉም ሊይዝ አለመቻሉን እውዱ በግልጽ ያመክተናል:: ይኸውም ሊያድን የሚችል መሆኑን በመግለጹ ነው:: ስለዚህም በውክልና ወደ እግዚአብሔር ይግባኝ ማለት የሚለው ትርጉም ለዚህም ክፍል ተስማሚና አውዳዊ ትርጉሙ መሆኑን መረዳት ይቻላል:: በዕብ. 9:24 ላይ ክርስቶስ አሁን *ስለ እኛ በአብ ፊት ይታይ ዘንድ* ወደ ሰማይ እንደ ገባ ይገልጻል:: ይህ አገላለጽ ደግሞ የበለጠ ምልጃ ተብሎ የተተረጎመውን ቃል ፅንሰ ሐሳብ የክርስቶስ ይግባኝ በውክልና በአብ ፊት መታየት እንደሆነ አጉልቶ የሚያሳይ ነው::

በወንጌላውያን የሥነ መለኮት ሰዎች ዘንድ የክርስቶስ ምልጃ ፅንሰ ሐሳብ ማድረግ የማይችል ለምኖ የሚያስደርግ በሚለው ትርጓሜ ጥቅም ላይ ሲውል አይስተዋልም፤ ይልቁንም ከአብ ጋር እኩል ሆኖ ሳለ በአድኅኖት ግብሩ ስለ አማኞች መታየቱ እንጂ:: ከዚህም የተነሣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ዘንድ:- «ፕሮቴስታንቶች ኢየሱስ ያማልዳል በማለት ከአምላክነቱ ዝቅ አድርገውት ከትንሣኤውም በኋላ ስለ ሰዎች ይማልዳል (ይለምናል) ይላሉ!!» የሚለው ድምዳሜም ሊታረም እንደሚገባውና እርስ በእርስ መማማር እንደሚያሻ መገንዘብ ያሻል:: በተለይ ደግሞ ስለምልጃ ምንታዌ (ሁለታዊነት ያለው) ትርጉም በማስተዋል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ክርስቶስ ስለ እኛ እንደሚማልድ የሚያወሱ ክፍሎች ከዐውዳቸው ፍታቴያቸውን እንዲይዙ በማድረግ የመስበክም ሆነ የማስተማርን አስፈላጊነት የሚያመለክት ነው::



### 3.1.3. ሥነ ፍጥረት

#### 3.1.3.1. ሥነ ፍጥረት በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ዓለምን ከምንም እንደፈጠረና ከእርሱም ሌላ አምላክ እንደሌለ ታምናለች:: ከዓለም ፍጥረት አስቀድሞ ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ይኖር እንደነበርም ታምናለች:: ሠይፈ ሥላሴ ስለ እግዚአብሔር ፈጣሪነትና ስለመፍጠር የተነሣሣበትን ምክንያት ሲገልጹ:- «ፈጣሪ ማለት ቅሉ አስቀድሞ በምንም ዓይነትና ቅርጽ ሕልውና ያልነበረውን ነገር ወደ መኖር ያመጣ ቅርጽና ዓይነት ሰጥቶ የገለጠ ማለት ነው፤ እግዚአብሔር ፍጥረትን መፍጠሩ በባሕርዩ ጉድለት ኖሮበት የሚያስፈልገው ሆኖ አይደለም፤ እግዚአብሔር ራሱ በራሱ ለመኖር የሚችል ስለ ሆነ ፍጹም ነው፤ በመሆኑም ለሕልውናው ሌላ ድጋፍ አያስፈልገውም::»[75]

ቤተክርስቲያኒቱ እግዚአብሔር ፍጥረትን በቀናት እንጂ በረዥም ዘመናት እንዳልፈጠረና ስድስት ቀን የተባለው በዘመን ከተተረጎመ ፍጥረት በአዝጋሚ ለውጥ (ኢቮልዩሽን) እንደሆነ ወደሚያምነው ፍልስፍና ሊያመራ መቻሉን ያላቸውን ስጋት በመንተራስ ሠይፈ ሥላሴ ይገልጻሉ:: ስለዚህም «በመጀመሪያው ቀን 7፥ በሁለተኛው ቀን 1፥ በሦስተኛው ቀን 4፥ በአራተኛው ቀን 3፥ በአምስተኛው ቀን 3፥ በስድስተኛው ቀን 4 ፍጥረታት ተፈጥረዋል፤ በድምሩ **22** ይሆናሉ (ዘፍ. 1:1-31)::» በማለት አስፍረዋል::[76]

[75] ሠይፈ ሥላሴ፥ የኢ.ኦ.ተ. ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖት እና...ገጽ. 14
[76] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ. 19

ለዚህ ትምህርት ምንጩ የአክሲማሮስ አስተርእዮ እንደሆነና አክሲማሮስ ስለ እያንዳንዱ ፍጥረት ማንነት ሲዘረዝር እሑድ ማለዳ በሥላሴ የተፈጠሩ ሰባቱ ፍጥረታት:- አራቱ ባሕርያት ማለትም እሳት÷ ነፋስ÷ ውሃ እና መሬት እንዲሁም ሰማያት÷ መላእክትና ጨለማ ናቸው:: እግዚአብሔር እሳትን «እኔ ሁሉን ቻይ ነኝ!» ሲል ነፋስን «እኔ ኃጢአተኛውን ከጻድቁ የምለይ ነኝ!» ሲል መሬትን ደግሞ «እኔ ሁሉን ቻይ ነኝ!» ሲል እንደፈጠረም ይገልጻል::[77]

### 3.1.3.2. ሰባቱ ሰማያት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር ሰባት ሠማያትን እንደፈጠረ ታምናለች:: ለዚህም መሠረቱ የአክሲማሮስ ኢጲፋንዮስ መገለጥ ሲሆን እንደ አክሲማሮስ አባባል:- በሦስተኛው ሰዓተ ሌሊት መንበረ ስብሐትን ከሰማያት በላይ እንደ ድንኳን እና አራት ጎኖች እንዳሉት መቅደስ መዘርጋቱን÷ በ4ኛው ሰዓተ ሌሊት ጽርሐ አርያምን እንደ ጠፈር በመንበረ ስብሐት ላይ መመሥረቱንና ከእግዚአብሔር ውጪ ማንም የጽርሐ አርያምን ወሰን እንደማያውቅ ገልጧል:: ኢዮር÷ ራማ እና ኤረር የተባሉትን ሰማያትም ከእሳት ክፋይ በ5ኛው÷ በ6ኛውና በ7ኛው ሰዓተ ሌሊት እንደፈጠራቸውም በመጥቀስ እነዚህ ሦስቱ ሰማያት በእግዚአብሔር ማሕተም እንደታተመባቸውና የመላእክት አገር በመባል እንደሚታወቁም ገልጧል:: እግዚአብሔር ለእነዚህ ሰማያት መስኮት ያላደረገላቸውም የእርሱን ምሥጢር ከመላእክት ለመሰወር

[77] መክብብ ግርማየሱስ አራማ÷ ሥነ ፍጥረት እንደ አክሲማሮስ... ገጽ 7-9



እንደሆነም ይናገራል:: በ10ኛው ሰዓተ ሌሊትም ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ፈጥሯል በማለት ያስረዳል::[78]

እንደ የአለቃ ኪዳነ ወልድ የግዕዝ መዝገበ ቃላት እነዚህ ሰባቱ ሠማያት በግዕዝ:- ኤረር÷ ራማ÷ ኢዮር÷ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት÷ ሠማውቱል÷ መንበረ መንግሥት እና ጽርሐ አርያም ሲሆኑ በዕብራይስጥ ደግሞ:- ዌሎን÷ ረቂይ÷ ሳሐክ ÷ ዚቡል÷ ሲያን ÷ ኒኮለ እና አርጎት ናቸው::[79]

### 3.1.3.3. የሰው ተፈጥሮ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የሰው ፍጥረቱ ከመላእክትም ሆነ ከእንበሳት ልዩ መሆኑን ታምናለች:: እንደ ሠይፈ ሥላሴ አገላለጽ:- «ሰው ረቂቅ ነፍስ ብትኖረውም መልአክ አይደለም፤ ግዙፍ አካል ቢኖረውም እንሰሳ አይደለም፤ ከመልአክም ከእንሰሳም የተለየ ነው፤ ሥጋዊና መዋቲ በመሆኑ ከመልአክ ይለያል፤ ነባቢት÷ ለባዊትና ሕያዊት ነፍስ ያለው በመሆኑ ከእንስሳ ይለያሉ::» ይላሉ[80]

የነፍስ ፍጥረቷ አንድ ጊዜ እንደተከናወነና ከዚያ በኋላ ግን ከእናትና ከአባት የምትከፈል እንደሆነችም የቤተክርስቲያኒቱን እምነት ሲያብራሩ:-

[78] መክብብ ግርማየሱስ አራሚ ሥነ ፍጥረት እንደ አክሲማሮስ... ገጽ 7-9
[79] አለቃ ኪዳነ ወልድ÷ አለቃ ኪዳነ ወልድ ግዕዝ መዝገበ ቃላት ገጽ 870
[80] ሠይፈ ሥላሴ የኢ. ኦ. ተ. ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖትና... ገጽ 22

«ለመጀመሪያ ጊዜ የሥጋ ተፈጥሮ ከመሬት ሲሆን ነፍስ ግን ከእግዚአብሔር የተሠጠች ናት፤ (መክ 12:7) ከዚህ በኋላ ነፍስ ከእናትና አባት ትከፈላለች እንጂ ሁልጊዜ አትፈጠርም፤ ከመዝገበ ነፍሳትም አትላክም።» የሰው በእግዚአብሔር ምሳሌ መፈጠርንም በተመለከተ «የእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ ማለትም ቅርጽና መጠን አይነትም ሳይሆን ዕውቀት፥ ቅድስና፥ ሥልጣን የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆኖ በምድር ላይ የፍጥረታት ገዢ መሆን ነፃ አእምሮና ዘለዓለማዊ ሕይወት ነው፤ ስለዚህ ክፋም ሆነ መልካም ለመሥራት ለሰው ነፃ ፈቃድ አለው።... ሰው ከመጀመሪያው ጀምሮ እሁን ባለው መልኩና ቅርጹ ፍጹም ሆኖ የተፈጠረ ነው፤ ... » በማለት ይገልጹታል።[81]

እንደ አክሲማሮስ አገላለጽ ሰው ከአራቱ ባሕርያት፡- ከመሬት ከውሃ ከነፋስና ከእሳት እንደተፈጠረ ይገልጻል። ስለ አፈጣጠሩም ሲተርክ፡-
ሥላሴ የተለያዩ ፍጥረታትን በየዕለቱ ከፈጠሩ በኋላ «ንግበር ሰብአ በአርያነ ወበአምሳሊነ» ቢሉት አዳም የ30 አመት ጎልማሳ ሆኖ ተፈጠረ። አዳምንስ ከምን ከምን ፈጠሩት ቢሉ ከእሳት፥ ከነፋስ፥ ከውኃ፥ ከመሬት እንደ ቅባኑግ ለይተው ቅጥራን አውጥተው እንደ ዘንግ መልምለው እንደ እሸት ፈልፍለው በርሳቸው አርአያ በርሳቸው አምሳያ ፈጠሩት። እሳትና ነፋስ ደመነፍስ ናቸው ካሉ፤ የመሬት ግብሩ ምንድር ነው ቢሉ ግዘፍ ነው። ይኸውም ሥጋ፥ ዚማት፥ ጽፍር፥ ፀጉር አካል የሚሆን መሬት ነው፤ የውሃስ ግብሩ ምንድር ነው ቢሉ ርቀት ነው ይኸውም ደም፥ እንባ፥ ምራቅ ሆኖ የሚፈስ ውሃ ነው።

[81] ሠይፈ ሥላሴ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖትና ... ገጽ 22



... ከዚያ በኋላ አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ ንፍሐተ መንፈስ ቅዱስ አሳደረበት፤ ... ከዚህ በኋላ አዳም ከሥላሴ የጸጋ ልጅነት እንደተወለደ የጸጋ መንግስት እንደነገሠ በምን ምሳሌ ይታወቃል ቢሉ በዚያ በተቀበለው መንፈስ ቅዱስ ሥላሴ በባሕርይ ያዘዙትን በጸጋ አዘዘ። ሔዋን በተፈጠረች በ80 ቀንዋ እንደ አዳም ከሥላሴ ልጀነት በጸጋ ተወለደች የጸጋ መንግሥት ነገሠች።[82]

### 3.1.3.4. የመላእክት ተፈጥሮ

መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ 13:15 ላይ፡- «ከእሳት ከነፋስ የፈጠራቸው እሱ እንደ ሆነ ስላወቁ እነሳቸው በተዋረደ ልቡና ፈጣሪያቸውን ያመሰግኑታልና ... እንዳንተ ካሉ ከመላእክት ሁሉ ተለይተህ ተዋረድህ። » በማለት የመላእክትን ተፈጥሮ የሠይጣንን አወዳደቅ ቢገልጽም መቼ እንደተፈጠሩ አያመለክትም። ሆኖም ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መላዕክት በመጀመሪያው ቀን እንደተፈጠሩ ታምናለች።

የመላእክትን መልክ እንዲህ ነው ማለት እንደማይቻልና ሲገለጡም አንዳንድ ጊዜ በሰው መልክ፤ ባለ ክንፍ፤ ክንፍ የሌላቸው ሆነውም ይታያሉ የሚልም እምነት አላት። በቀኖና መጻሕፍት ከተጠቀሱት ከገብርኤልና ከሚካኤል በተጨማሪ በጦቢትና በሄኖክ መጻሕፍት በስም የተጠቀሱ ሩፋኤል፥ ዑራኤል፥ ራጉኤልና ፋኑኤል የሚባሉ መላእክት እንዳሉም ታምናለች።

[82] መክብብ ግርማ ኢየሱስ (አራሚ) ሥነ ፍጥረት እንደ አክሲማሮስ ገጽ. 151 እና 159

የአክሲማሮስ መጽሐፍ መላእክት አራት አለቃ አርባ ነገድ እንደሆኑና የመጀመሪያዎቹ ዐሥር ነገዶች ስማቸው አጋዕዝት ሲባሉ አለቃቸው ሳጥናኤል እንደሆነ ይገልጻል፡፡ የስሙ ትርጉምም ቅሩበ እግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ ሁለተኛው ምድብ ላይ ዐሥር ነገዶች ኪሩቤል ሲባሉ ግብራቸውም እንደ ካህናት ነው፡፡ ከወገባቸው በላይ 44 ከወገባቸው በታች ደግሞ 11 ናቸው ራሶቻቸውም እንደ ሰው+ አንበሳ+ ንስር እና በሬ ነው፡፡ ዐይኖች የሞሉባቸው ናቸው፡፡ ሦስተኛ የሚገኙት ዐሥር ነገዶች ደግሞ ሱራፌል ሲሆኑ 76 ክንፎችና 77 እጆች አሏቸው፡፡ አገልግሎታቸውም ዲያቆናት ናቸው፡፡ከአለቃቸው ከሚካኤል ጋር በአራተኛው ሰማይ በኢዮር ይገኛሉ፡፡

በ5ኛው ሰዓት እግዚአብሔር በራማ ያሉትን መላእክት ወደ ሦስት አለቃና 30 ነገድ ከፈላቸው፡ የመጀመሪያዎቹ 10 ነገዶች አርባብ ሲባሉ አለቃቸውም ገብርኤል ግብራቸውም የሥላሴ እልፍኝ አስከልካይ ሲሆን የሠፈሩትም በላይኛው ከተማ በራማ ነው፡፡ ሁለተኛ ዐሥር ነገድ እንደ ነፋስ የሚያበሩ መናብርት ሲባሉ አለቃቸው ሩፋኤል በግብራቸውም የሥላሴ ጋሻ ጃግሬ ናቸው፡፡ ሦስተኛዎቹ አስር ነገዶች ሥልጣናት የሚባሉ ሲሆን አለቃቸው ሱርየል መልእክ ነው፡፡ በግብራቸውም የእምልኮ መሪዎች ናቸው፡፡ የሠፈረሩትም በሦስተኛው የራማ ከተማ ነው በማለት በኢዮርና በራማ ያሉት መላእክት በአጠቃላይ 79 ነገድ እንደሆኑ በመግለጽ ከእስቆች አንዱ ከአዳም ዘር ጋር አንድ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡[83]

[83] መክብብ ግርማ ኢየሱስ (አራሚ) ሥነ ፍጥረት እንደ... ገጽ: 17-25



### 3.1.3.5. እንማማር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥነ ፍጥረት ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው መረዳት ላይ ተጨማሪ መገለጥን በማካተት ማብራሪያ በመሥጠት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ የተሟላ የሥነ ፍጥረት መረጃን አይሰጥም፡፡ እንዲያውም ሙሴ ኦሪት ዘፍጥረትን የጻፈበት ዓላማ የፍጥረትን ታሪክ ስመዘገብ እንዳልሆነ የታሪካዊ ደሃራ ማስረጃዎች ያመለክቱናል፡፡ ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሙሴ እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ገዢና እስራኤላውያንንም ከነበሩበት ውጥንቅጡ የወጣ ሕይወት እንደሚያወጣ ለማመልከት ምድርን ባዶ ከሆነና ውጥንቅጡ ከወጣ ሁኔታ እንዳወጣት በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ላይ አበከሮ ይገልጻል፡፡

ስለዚህም እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ፍጥረት የተሟላ መረጃን ሰጥቶን ቢሆን መልካም፤ ያለዚያ ግን በመገለጥ ስም የሚጨመሩ አሳቤዎች እስትንፋስ እግዚአብሔር እንዳለባቸው ተደርገው የሚቆጠሩ ከሆነ አደጋው የከፋ ነው፡፡ ስለዚህም ለአስተምህሮ መሠረት ተደርገው መወሰድ የለባቸውም፡፡ በዚህ ላይ አንዳንድ የሥነ መለኮት ምሑራን የጥንታዊ ግሪክ አፈታሪክ (Greek Mytheology) ወደ ክርስትና እምነት እንደተጠመቀ አመልካች መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም ግን በእኔ እምነት በእስትንፋስ እግዚአብሔር እንደተጻፉ ከሚታመንባቸው የቀኖና መጻሕፍት ውጪ በመገለጥ ስም የተጻፉትን መጻሕፍት ለተጨማሪ የታሪክና የሥነ ጽሑፍ ባሕርያት ጥናት ማስረጃ ካላቸው ጠቀሜታ ውጪ ስለማይኖራቸው ያልተገለጹልንን ምሥጢራት ለአምላካችን

ለእግዚአብሔር በመተው የተገለጠውን እውነት ተመርኩዘን መንዝ ይኖርብናል።

### 3.1.4. ኃጢአትና ድኅነት

#### 3.1.4.1. ስለ ኃጢአት ምንነት ያላት ግንዛቤ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ስለ ኃጢአት ምንነት ያላትን ትምህርት ከኃጢአት ጅማሬ በመነሳት ስንመለከት በአንድ ሰው በአዳም ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም እንደገባ ታምናለች። የሰው ልጆች ሁሉ በአዳም ምክንያት የእርሱን በደል በመውረሳቸው በሁለት መንገድ ማለትም በአዳም እና ራሳቸው በሚፈጽሙት ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት እንደሚጠየቁ ታምናለች። እንደ ሠይፈ ሥላሴ አገላለጽ :- «...(አዳም) የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፈ ይህም ኃጢአት ለዘርው ሁሉ ተላልፎአል፤ በኃጢአት ከወደቀና ከተረገመ ለሰይጣን ተገዥ ከሆነ በኋላ ወልዶአቸዋልና ልጆቹ ሁሉ እንደራሱ ኃጢአተኞች ሆነዋል፤ (ዘፍ 5:3) የአዳም በደል የመጀመሪያ እንደመሆኑ "ጥንተ አብሶ" ሲባል ለሁሉም በመተላለፉ ደግሞ "የውርስ ኃጢአት" እየተባለ ይጠራል፤...»[84]

ሰው ሁሉ በአዳም ኃጢአት ተጠያቂ ስለመሆኑ በተለይ ደግሞ የጌታችን እናት ቅድስት ማርያምም ጥንተ አብሶ እንደነበረባት ሲገልጹ:- «አንዳንዶች እመቤታችን እድፎ የነበረው የአዳም ጠባይ ወይም ጥንተ አብሶ እንደሌለባት ያስተምራሉ፤ ነገር ግን ይህ ትምህርት በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን ተቀባይነት የለውም፤ ምክንያቱም

[84] ሠይፈ ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖት እና ... ገጽ 23



እመቤታችን ከኢያቄምና ከሐና በሩካቤ ዘበሕግ የተገኘች ናት እንጂ ከሰማይ የወረደች የመላእክት ወገን አይደለችምና፤ ካሣ የማያስፈልጋትም ሳትሆን ክርስቶስ በደሙ ከዋጃቸው ካሣም ከተከፈለላቸው ወገን ናት፤ ሆኖም እንደ አዳምና ሔዋን የምኞት የመናገር የገቢር ኃጢአት ፈጽሞ የለባትም።» ይላሉ።[85]

ከዚህ የምንረዳው ደግሞ የሰው ዘር ሆኖ ጥንተ አብሶ የሌለበትና የክርስቶስ ሞት ከአዳም ለወረሰው በደል የማያስፈልገው እንደሌለ ነው። ስለዚህም በአንዱ በአዳም ምክንያት ሰዎች ሁሉ በደለኞች እንደሆኑና የውርስ ኃጢአትንም በመቀበላቸው በራሳቸው ከኃጢአት ነፃ እንዳይደሉ የቤተ ክርስቲያኒቱ እምነት እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

#### 3.1.4.2. ስለ ድኅነት ያላት ግንዛቤ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሁሉ በአዳም ምክንያት ኃጢአተኞች እንደሆኑ ስታምን የክርስቶስ ሞት ከጥንተ አብሶ (Original Sin) ድኅነትን እንዲያገኙ የተፈጸመ እንደሆነ ታምናለች። የክርስቶስን ሞት በተመለከተ ሠይፈ ሥላሴ ሲገልጹ:-«የክርስቶስ ሞት የነፍስና የሥጋ መለየት ነው፤ በሃይማኖት ትምህርታችን ክርስቶስ ሞተ ባልን ጊዜ ሥጋ ብቻ ሳይሆን መለኮትም በሥጋ ሞተ ብለን እናምናለን፤ የዕሩቅ ብዕሲ ሞት ብቻ ሊያድን አይችልምና፥ (1ኛ ጴጥ. 3:18)»[86]

[85] ሠይፈ ሥላሴ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖተ እና ... ገጽ 29

[86] ዝኒከማሁ ገጽ 26

በክርስቶስ ያመኑ ክርስቲያኖች በምኞት በንግግርና በተግባር ለሚፈጸም ኃጢአት ሥርየትን ለማግኘት ሊያደርጓቸው የሚገባቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ስለዚህም የኃጢአት ሥርየትንና ዘላለማዊ ድኅነትን ለማግኘት ሰዎች ስለ ኃጢአታቸው ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፦

እንደ ቤተክርስቲያኒቱ አስተምህሮ ጥምቀት ወደ ቤተክርስቲያንና ወደ መንግሥተ እግዚአብሔር መግቢያ በር ሲሆን፤ (ዮሐ. 3:5) ከጥንተ አብሶ የኃጢአትን ሥርየት ከማግኘት ጋር የሚያያዝ ነው። ስለዚህም ሕጻናት በጥምቀት የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾች መሆን እንደሚችሉ ያስው አስተምህሮም ከጥንተ አብሶ ውጪ በራሳቸው የፈጸሙት በደል ስለሌለባቸው ነው። ስለዚህም ሕጻናት ቅዱስ ቁርባንን መካፈል ይችላሉ። ይህ ደግሞ የዘላለም ሕይወት እንደሚያሰጣቸው ይታመናል።

በሌላ በኩል ደግሞ ምዕመናን ዘላለማዊ ድኅነትን ለማግኘት ስለ ኃጢአታቸው ማድረግ የሚገባቸው በርካታ ነገሮች አሉ። ጾምና ፀሎት÷ መልካም ሥራ ÷ሕግጋትን መጠበቅ÷ ቅዱስ ቁርባንን (ሥጋወ ደሙን) መቀበል÷ ሲሞቱ ጸሎተ ፍትሐት ማስደረግ ወዘተ ሲሆን ዓለምን ንቆ በምንኩስና ለመኖር መወሰን ትልቅ ጽድቅ ተደርጎ የሚቆጠር ነው።



### 3.1.4.3. እውነትን የሸፈነው አመድ ይርገፍገፍ

በዓለማችን ኢትዮጵያን በብስራተ ወንጌል የሚቀድሟት አገሮች ስለመኖራቸው አጠያያቂ እስኪሆን ድረስ ከጌታ ሐዋርያት እስከ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን እናትነት ያሉት በኢትዮጵያ የነበራቸውን አስተዋጽኦ መመልከት በቂ ነው። በዚህም ረገድ ሊነሣ የሚገባው ጥያቄ በውኑ በጌታ ሐዋርያት ወንጌል እንደተበሰረላትና ከቀደምት የሃይማኖት አባቶች ሥርዓተ ክርስትናን እንደተቀበለች የሚነገርላት አገራችን ኢትዮጵያ የተበሰረላት ወንጌል ንጹሑ የክርስቶስ የምሥራች ነበርን? የተቀበለችውስ ምን አይነት ክርስትና ነበር? የሚል ነው።

ወንጌል ለኢትዮጵያ በሐዋርያት የተሰበከና ቤተክርስቲያንም ለተዋሕዶ አስተምህሮቷ የእስክንድርያዋ ቤተክርስቲያን አባት የቅዱስ ቄርሎስን የሃይማኖት መግለጫ እንደተከተለች የምታምን ናት። እንግዲህ ከጌታ ሐዋርያት የወንጌልን የምሥራች ከመቀበሏም ባሻይ በምንም ያልተበረዘውን ትኩሱን የምሥራች (ወንጌል) በቀደምት ዘመናት ተቀብላለች። ከዚህም የተነሣ ከቤተክርስቲያኒቱ ታሪክ እንደምናስተውሰው ወንጌልን ከምንጩ የተቀበለች ከመሆኗም ባሻገር የንጹሑ ወንጌል ሰባኪ እንደነበረች መረዳት አያዳግትም።

በአንዳንዶች እምነት ወንጌል የደረሰውን በወንጌል መድረስ (Evangelizing the Evangelized) በሚል አመለካከት ኢትዮጵያ የክርስቲያን ሀገር በመሆንዋ ወንጌል ሰባኪያን አያስፈልጓትም ለማለት የሚጠቀሙት አባባል ነው። በምዕራቡ ዓለም ለሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከውስጧ የወጡ መነኮሳቶቿ፦ «መንገድ ስተሻል! ንጹሑን

ወንጌል በትውፊት ከድንሻል! ስለዚህም አመዱን በማራገፍ [illegible] ሰፍራውን ይያዝ!!» ብለው ተነስተው ነበር:: ይህ የሚያስተምረን ደግሞ ከትክክለኛው መንገድ የወጣች ቤተክርስቲያን ሁሌም ቢሆን ወደ መንገዷ አንድትመለስ እግዚአብሔር ሰዎች እንዳሉት ነው::

ስለዚህም በዓለማችን አንቱ ለመባል የበቃች የሀገራችን ቤተክርስቲያን የዕድሜ ብዛት እንድትጃጅ ሳይሆን እንድትከበርና አሁንም ምሳሌነቷን ጠብቃ ወንጌልን በትኩስነቱ ለዓለማችን በማድረስ ረገድ ታላቅ አስተዋጽኦዋን እንድታበረክት ሊያደርጋት ይገባል:: ሆኖም ግን በእጇ ያለው ወንጌል ተልዕኮዋን ለመወጣት የሚያስችል ኃይሉን የጠበቀና በእርግጥ በትኩስነቱ እንዳለ ይሆንን? ለዚህ ጥያቄ ምላሹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ወቅታዊ አንቅስቃሴ አንደ ሮሟ ቤተክርስቲያን በገድላት በተሳሰፈና በንጹሑ ወንጌል ላይ በተነዛ አመድ ፍሙ እንደተዳፈነ የሚያረጋግጥ ነው:: የአመዱ እድሜ መቁጠርም የፍሙን ፍምነት አጠያያቂ አያደረገው ነው:: ከዚህም የተነሣ በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተፈተነና ራሱንም እንዳያስገዛ ብዙ ጠበቃዎች ያሉትን የተገለጠልኝ ባዮችንና «በቁ» በተባሉ ሰዎች ስም በተለያዩ ጊዜያት የተጻፉ መጻሕፍት ንጹሑን ወንጌል አመድ አልብሰውታል::

ለዚህ ደግሞ ታሪክ እንደሚያስረዳን በዮዲትና በመሐመድ ግራኝ አማካኝነት በሀገራችን የወደሙ ቅዱሳት መጻሕፍትን አስታክኮ የገድል ደራሲያን መፍሰቅ ተጠቃሽ ነው:: ከዚህ በተያያዘም አንደ ዘርዓ ያቆብ ያሉ ነገሥታት ለእነዚህ መጻሕፍት ትምህርት ያሳዩት ጥብቅና ለንጹሑ ወንጌል መሰበክ የቆሙትን እነ አባ አስጢፋኖስን በሀይማኖት ቅናት ስም ከምድረ ገጽ ማጥፋት ንጉሡን በአማላጅነት ስፍራ እንዲቀመጡ እንዳደረጋቸው የሚታመንባት አገር ናት::



እንግዲህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከንጹሑ ወንጌል ወደ ገድል፥ ከቀዳሚ የምሥራች ተቀባይነት ወደ ኋለኛነት የተንሸራተተችና በአሁኑም ወቅት ወንጌልን በምድራችን ቀድሞ ወደ ነበረው ስፍራው እስካልመለሰችው ድረስ የክርስቶስ አምባሳደርነቷን ለ«ቅዱሳን» ባላት አምባሳደርነት መሰወሟ ግልጽ ነው:: ስለዚህም የቤተክርስቲያኒቱን ዕጣ ፈንታ በሁለት አቅጣጫ መመልከት ይቻላል::

የመጀመሪያው በአፍቅሮተ መጻሕፍት ስም በክርስቶስ ወንጌል ላይ የተጫነውን አመድ ማራገፍና ፍሙን ማራገብ ነው:: ይህ ደግሞ ቤተክርስቲያኒቱ «እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ ንሠሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንሰሐም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ::» (ራዕ. 2:5):: በሚለው መሠረት ከክርስቶስ መስቀል መውደቋን በማስተዋልና ንሠሐ በመግባት ለወንጌል ቅድሚያውን በመስጠት የሰዎች ድነት ሊገዳት ይገባል:: ባህለ ሃይማኖቷን ጠብቀው ከጊዜ በኋላ ወደ ቤተክርስቲያኒቱ የሰረጉትንና በኑፋቄነት የሚፈረጁ ትምህርቶችን ለታሪክ ቤተመዘክር በማስገባት ለሃይማኖት ትምህርቶቿ ወደ ቀኖና መጻሕፍቷ መመለስ ይኖርባታል::

በሌላ በኩል ደግሞ ለሰርዴስ ቤተክርስቲያን በተነገረው:- «ሥራህን አውቃለሁ ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ ሞተህማል::» ራዕ.3:1 የሚል የትንቢት መልእክትነቱ የዛሬይቱንም ቤተክርስቲያን የሚወቅስ እንደሆነ በማስተዋል ቤተክርስቲያን ከመባሏ ባሻገር ለጥንቆላው፥ ለአስማቱና ለመተቱ ስፍራ ለቀቃ ሕዝቤ የምትለው ብዙሆኑ ከአርባ ወይም ከሠማንያ ቀኑ ውጪ ሲሞት ካልሆነ በስተቀር ወደ እርሷ

የማይመጣና የክርስትናን ስም በመስጠት ብቻ ክርስቲያን ብላ የምታውቀው ነው። ከዚህም የተነሣ የሃይማኖት ብሬ ይመስል ከዚህም ከዚያም በቃረመውና ወንጌል ባልገራው አህዛባዊ ልምምድ ውስጥ እውነቱን ሳያውቅ «የቄስ ቄስ ዘር ነኝ!» የሚል ትምክህት ያለው ቁጥሩ ብዙ ነው። ለዚህ ሕዝብ ደግሞ የአርባና የሠማንያዋን ቀን ጥምቀቱን እስቦ ምናልባትም በአንገቱ ላይ ክር ማስሩን አይቶ ወንጌልን በዚህ መተርጎም መሣሣት ነው። ስለዚህም ለእንዲህ ዓይነቱ በክርስቲያን ስም የሚጠራ አረማዊ የክርስቶስን የእድኅኖት የምሥራች የሚያበሰረውን ወንጌል መስበክ የግድ ነው።

### 3.1.4.4. እንማማር

በጥንተ አብሶ (Original Sin) ዙርያ በርካታ ክርክሮች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ የአዳም ኃጢአት ለሰው ዘር የተወረሰው እንዴት ነው? የኃጢአት ውርስ ሲባል ምን ማለት ነው? የሚሉ ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩሩ ነጥቦች ይገኙበታል።

በዓለማችን እያንዳንዱ የኃይማኖት ድርጅት ስለ ጽድቅ ባለው ጥማት ኃይማኖተኛ በመሆንና ይህንንና ያንን በማድረግ ጽድቅ እንደሚገኝ ሲያምንና ሲያሳምን ይገኛል። ከንጹሑ ወንጌል ውጪ ሁሉም ይህንንና ያንን በማድረግ ጽድቅ ይገኛል የሚሉባቸው ሕግጋት አሏቸው። ቤተክርስቲያን መባልን ሳይሆን ንጹሑን ወንጌል መስበክ ያቆመች ቤተክርስቲያንም ለጽድቅ ይሆናሉ በማለት ስትሰብካቸው የነበሩ በርካታ ሕግጋት የነበሯት የምዕራቧ ቤተክርስቲያንም ለጽድቅ በርካታ



መስፈርትን ስታወጣ ኖራለች። የምሥራቹ ተቀብሮበት እንዳይቀር የወደደ እግዚአብሔር ግን በየዘመናቱ ለስማዕትነት የተዘጋጁ ሰዎችን በማስነሣት ወደ መንገዱ ሲመልሳት አልቦዘነም።

ይህንን ሳስብ በአንድ በምዕራቡ ዓለም የተፈጸመና በምዕራቧ ቤተክርስቲያን መነኩሴ የነበሩ ሰው ታሪክ ትዝ አለኝ። እኚህ ሰው በምንኩስና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ከሚጥሩቱ ወገን የነበሩ መነኩሴ ናቸው። በገዳም ሕይወታቸው ሁል ጊዜ የሚራቡትና የሚጠሙት ጽድቅን ማግኘት መቻል ነበር። ታዲያ ገዳም ውስጥ ሳሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት ያነቡ ጀመር። በተለይም ደግሞ ለሮሜ ሰዎች የተጻፈውን የሐዋርያው የጳውሎስን መልዕክት ሲያነቡ የእግዚአብሔር ቁጣ በሰው ዘር ሁሉ ላይ እንደሚገለጥ፥ አይሁድ ቢሆን አህዛብ ሁሉ ኃጢአትን ስለ ሠራ ከፍርድ እንደማያመልጥ ያስተውላሉ። በዚህን ጊዜ፦ «መሐሪን አምላክ የት አገኛለሁ?» የሚልን ጥያቄ ራሳቸውን ይጠይቁ ጀመር። እኚህ መነኩሴ በሮሜ መልእክት ንባባቸው ወቅት፦ «- - የእግዚአብሔር ጽድቅ- - - » (ሮሜ. 1:17) የሚለው ለጥያቄያቸው ታላቅ ምላሽ ያዘለ ነበር።

ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ ሕግ ያላቸው አይሁድም ይሁኑ ሕግ የሌላቸው አህዛብ የሰውን ዘር በሙሉ ጽድቁ ብሎ የሚመካበት የሌለው መሆኑንና የሁሉንም ኃጢአተኝነት ብቻ ሳይሆን ትክክለኛውንም የጽድቅ መንገድ አስፍሯል። ነገር ግን ለሰው አዕምሮ አዳጋችና ለጽድቅ የመሆን ብቃቱን በእምነት ካልሆነ በቀር በካሣ ሕግ የማይገኝም በመሆኑ ለመቀበል ሞኝነት ይመስላል። ለእኚህ መለኩሴ የበራው ብርሃን ለካስ ጽድቅ የሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር የራሱ የሚል ነው። እሳቸው

(የወር አበባ የነካው ሞዴስ) ነው (ኢሳ. 64:6)። ስለዚህም ይህንን ንጹሑን ወንጌል የሚቃረን ሰው ሰራሽ ጽድቅን ስለማቆም የሚያጥሩ ትውፊቶች በሙዝየም ውስጥ በታቸውን እንዲይዙ ማድረግ ይጠበቅብናል።

### 3.1.5. ቤተክርስትያን በተዋሕዶ ግንዛቤ

#### 3.1.5.1. ስለ ቤተክርስቲያን ማንነት ያላት ግንዛቤ

ስለ ቤተክርስቲያን ያለው ትርጉም የክርስቲያኖች መሰብሰቢያ ቤት የሚል ነው። ስለዚህም ለአምልኮ ክርስቲያኖች የሚሰበሰቡባቸው ቤቶች ቤተ ክርስቲያናት እንደሆኑ በብዙዎች ዘንድ ሲነገር ይደመጣል።

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ልክ ቤተሰብ እንደሚለው ቃል ስለ ህንፃ ሳይሆን ስለ ሰዎች ስብስብ የተነገረ እንደሆነ መረዳት ያሻል። ቤተሰብ ማለት እናት፥ አባት፥ ልጆች እና አብረው የሚኖሩ ሌሎችንም ሰዎች ሊያካትት የሚችል እንደመሆኑ መጠን ቤተ ክርስቲያን የሚለውም ቃል የአማኞችን በብስብ የሚያመለክት ነው። ስለዚህም በተለምዶ ካለው መረዳት ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊው የቤተክርስቲያን ትርጉም መመለስ ያሻል።

#### 3.1.5.2. የቤተክርስቲያን ተከላ ስልቶቿ

በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ስትቋቋም በአራት ሀገረ ስብከት ተዋቅራ እንደ ነበር ይነገራል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በማዕከላዊነት በቅዱስ ሲኖዶስ የምትመራ ሲሆን በሀገረ



ስብከት ደረጃም የቤተክርስቲያን ተከላን ታካሂዳለች። በተለይ የቤተክርስቲያን ተከላ ሂደቷ ወደ አዳዲስና ቤተክርስቲያን ወደ ሌለበት ስፍራ ለመግባት የምዕመናኗን ጥያቄ ከአረት የአምልኮ ሥርዓት ጋር በተያያዘ የኮረብታማ ስፍራዎች የቦታ ምርጫን መሠረት ያደረገ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ አዳዲስ ቤተክርስቲያናት ትኩረት እንዲሰጣቸው ሊያደርግ በሚችል መልኩ ስያሜን ትሰጣለች። አብያተክርስቲያናቱ በቅዱሳን ስም የሚሰየሙ ሲሆን ይህ ደግሞ ምዕመናን ለቅዱሳኑ ካላቸው ክብር አንጻር አዲስ ወደ ተተከሉት አብያተክርስቲያናትም እንዲሄዱና እንዲያጠናክሩአት ያደርጋቸዋል። አብዛኛውን ጊዜም አዳዲሶቹን አብያተክርስቲያናት ሕዝብ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጣቸውን ቅዱሳን በደባል ስያሜነት መጠሪያቸው ያደርጉላቸዋል። ለዚህ ደግሞ ከአሪት የተወረሰ የታቦት ሥርዓት መኖሩ በመሠረታዊነት የሚጠቀስ ነው።

በተለይ ደግሞ ህዝብን ተከትላ የቤተክርስቲያን ተከላን በከተሞችና ከኢትዮጵያም ውጪ የምታከናውን ሲሆን አማኞቿ በሌሉባቸው ስፍራዎች ያለው እንቅስቃሴ ግን እንብዛም ነው። ይህ ደግሞ የቀድሞ ነገሥታት ለሌሎች ሚስዮናውያን የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በሌለችበት እንዲሰብኩ ከሰጡት መመሪያ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል።

#### 3.1.5.3. እንማማር

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በተለምዶ በተያዘው የቤተክርስቲያን ምንነት እንጂ ማንነት ያልሆነ ከሕንፃ ጋር የተቆራኘ ትርጉምን አክርራ ትይዛለች። ይህ ደግሞ ቤተክርስቲያን እንደ ቤተሠብ

ያለ የአማኞች አንድነትና ኅብረትን አመልካች መሆኗንና የቤተክርስቲያን ማንነት የአማኞች ኅብረት መሆኗን የማያካትት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም በሐዋ. ሥራ 20:28 እግዚአብሔር በገዛ ደሙ የዋጃት እንደሆነች ሲናገር ሕንፃን ሳይሆን ሕዝቧን እንደሆነ ማስተዋል ያሻል። ይህ ዓይነቱ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነታ ጋር የማይስማማ የቤተክርስቲያን ምንነት አሳቤ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ዘንድ የሚንጸባረቅ ሲሆን ክርስቶስ ደሙን ያፈሰሰላት ቤተክርስቲያን ሕንፃ ሳትሆን በክርስቶስ ያመኑ የክርስቲያኖች ኅብረት ስመሆኗ ተገቢ ትኩረት መስጠት ያሻል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የቤተክርስቲያን ተከላ አርያነቱ በተሰይ ያሏትን ምዕመናን ስመያዝ ከሚደረግ ጥረት አንጻር ጥሩ ስልት ነው። ሆኖም ግን እንደ አቡነ ተክለ ኃይማኖት ካሉ ቀደምት የቤተክርስቲያኒቱ ቅዱሳን ታሪክ በቀጣይነቱ ወንጌል ወዳልደረሰባቸው ስፍራዎች በሐርያዊ ተልእኮ የመግባቱ ሁኔታ እንብዛም ነው።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የእረኝነት ተግባርን በተመሰከተ ቤተክርስቲያኒቱ ሐዋርያዊ ተልዕኮን እየተወጣች ነውን?! የሚልን ጥያቄ የሚቀሰቅስ ነው። ብዙዎች በፆም ወራት መንፈሣዊነት የተስማቸው ቢመስሉም በቃስ እግዚአብሔር ታንፀው ስእግዚአብሔር መኖር የሚያስችል ሕይወት መምራትን በተመሰከተ የሚደረግ ጥረት የለም ቢባል ውሸት አይሆንም።



### 3.1.6. ምጽዓተ ክርስቶስና የዓለም ፍጻሜ በተዋሕዶ ግንዛቤ

#### 3.1.6.1. ምጽዓታዊ አሳቤዎች በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የጻድቃንም ሆነ የኃጥእን የሁሉም አካል በመቃብር እንደሚያድር የቅዱሳን ነፍስ በገነት የኃጥእንም ነፍስ በሲዖል እንደሚቆይና በመጨረሻም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሕያዋንና በሙታን ስመፍረድ ሲመጣ ሁሉም በአካል ትንሣኤን እንደሚያገኙ ታምናስች። ስለ ሥጋ ትንሣኤም ያላት እምነት፡- «ሥጋ አሁን ባለው መልኩ አይነሣም ትንሣኤ በተሐድሶ ነውና ጉድለት ያለበት አካል ሁሉ በጉድለቱ አይነሣም በትንሣኤ ጊዜ ረዥምና አጭር ጥቁርና ቀይ አይኖርም፤ ዛሬ ያለው የሥጋ ፍላጎት ሁሉ ያን ጊዜ አይኖርም፤ ከትንሣኤ በኋላ ሰዎች ሁሉ እንደ መላእክት ሆነው ይኖራሉ፤(ማቴ. 22:30፤) ዛሬ ነፍስ በሥጋ እንዳለች ሁሉ ኋላ ሥጋ በነፍስ ይኖራል።»[87]

ከዚህ በተጨማሪም ትንሣኤ ሙታን አንድ ጊዜ እንደሆነና ጻድቃን ፈጣሪያቸውን ክርስቶስን መስለው በክብር ሲነሡ፤ ኃጥአን ግን አለቃቸውን ሰይጣንን መስለው ለሃሳር ይነሣሉ፤የአመጣጡ ሁኔታም በመላእክት ታጅቦ የተሰቀለበት መስቀል በሰማይ ላይ እየታየ (ማቴ. 24:30) ይመጣል በማለት ስለ ምጽዓቱ ይገልጻሉ።[88]

ስለ ጌታ ምፅዓት በኢትዮጵያ ከተከናወኑ ክንውኖች ውስጥ አባ ጎርጎርዮስ በዐፄ ዘድንግል ዘመነ መንግሥት ሐሳዊ መሲሕ ተገልጦ

[87] ሠይፈ ሥላሴ የኢ. ኦ. ተ. ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት ገጽ 48
[88] ሠይፈ ሥላሴ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖት... ገጽ. 49-52

እንደነበር ሲተርኩ፦ "በአማራ ክልል (ሳይንት) እኔ ክርስቶስ ነኝ የሚል ሐሳዊ መሲሕ ተነሥቶ ነበር። የዚህ ሰው እናቱ መርዓተ ወንጌል ትባላለች። አባቱ ግን አይታወቅም። ጌታ ክርስቶስ ያደረገውን በማስመሰል 12 የሐሰት ቅዱሳት እንስት (ሴቶች) መርጦ ትምህርቱን ያስራጭ ጀመር። ንጉሡ ይህንን ሰምተው ወታደር ልከው እስያዙት፥ በዚህ ጊዜ ጭፍሮቹ ሁሉ ተበታተኑ፤ እሱም ወደ ንጉሡ ፊት ቀርቦ ቢጠየቅ አዎ፤ እኔ ክርስቶስ ነኝ፤ ከድንግል ማርያም ተወልጄ ሞቼ ተነስቼ ወደ ሰማይ ዐርጌ ነበር። ከቤተ እሥራኤል በመወሰዴ እሥራኤል ያልሆኑት ሁሉ ባዕድ አደረገን እንዳይሉኝ አሁን ደግሞ ከቤተ አሕዛብ ከምትሆን ከመርዐተ ወንጌል ተወለድኩ አላቸው። እርሳቸውም፦ 'ሰይጣን በሰው እያደረ እንዴት ይጫወትብናል' ብለው በሰይፍ እንዲቀጣ አደረጉ"[89]

#### 3.1.6.2. እንማማር

ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ግልጽና የማያወዛግብ ነገር ቢኖር የክርስቶስ ምጽዓት እርግጠኝነት ነው። ስለ አመጣጡም ያለው እውነታ በአካል እንደሆነና የሚመጣውም ሰፍርድ መሆኑን ነው።

ስለ ትንሣኤ አካል የማይሞት አካል መሆን ባሻገር የኃጥአን ትንሣኤ አለቃቸውን ሰይጣንን መስሰው፥ የጻድቃን ትንሣኤ ደግሞ ክርስቶስን መስሰው እንደሆነ ያሰውን ገላጸ በመጽሐፍ ቅዱስ ማስደገፍ የሚቻል

[89] አባ ጎርጎርዮስ፥ የኢት. ኦ. ተ. ቤተ ክርስቲያን እምነት ገጽ 50



አይመስለኝም። ሆኖም ግን ኃጥአን ሲፈረድባቸው ጻድቃን ደግሞ ሲፈረድልቸው ትንሣኤ ሙታን እንዳለ መረዳት እንችላለን። በአንዳንድ ክርስቲያኖች ዘንድ ትንሣኤ ከጊዜ አንጻር ምንታዌነት (ሁለትነት) እንዳለውና አስቀድሞ የጻድቃን ትንሣኤ እንዳለ ከዚያም የኃጢአን ትንሣኤ እንደሚሆን ያለውም አሳቤ ሙሉ በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ተደግፎ ማስረዳት አይቻልም። ለዚህ መሠረት የሚሆነው ደግሞ ከሺህ ዓመት መንግሥት ጋር ያለው የአሳቤ ቁርኘት ነው።

ስለዚህም ክርስቶስ በእርግጥ በአካል እንደሚመጣ እንጂ በአመጣጡ ላይ ያሉ የቅደም ተከተል እርከኖች በእርግጠኝነት መናገርም ሆነ የትንሣኤ ልዩነትን መናገር የሚያስችለን የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ አይኖረንም። ከዚህም የተነሣ ይህ እግዚአብሔር ሰራሱ ምሥጢር ካደረጋቸው ነገሮች አንዱ በመሆኑ የልዩነት መሠረት ሊሆን አይገባም።

## 3.2. የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ቅዱሳት ሥርዓቶቿ

### 3.2.1. ትእዛዛዊ መመሪያ ያላቸው ሥርዓቶች

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን ሰመባል ከሚታወቁት ውስጥ ሁለቱ ትዕዛዛዊ መመሪያ ያላቸው በመሆኑ ሁሉም አብያተክርስቲያናት ይጋሯቸዋል። እነርሱንም፦ ምሥጢረ ጥምቀት እና ምሥጢረ ቁርባን ትላቸዋለች።

#### 3.2.1.1. ጥምቀት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጥምቀት በምሥጢረ ሥላሴና በምሥጢረ ሥጋዌ ስሚያምኑ የሚፈጸም ቅዱስ ሥርዓት

እንዲሁም የኃጢአት መደምሰሻ፥ የመንግሥት ስማያት መውረሻ እንደሆነ ይታመናል:: ምሥጢር የተሰኘበትም ምክንያት ካህኑ ጸሎቱን እንዳጠናቀቀ ለማጥመቂያ የተዘጋጀው ውሃ ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ ጎኑ በጦር ሲወጋ እንደወጣው ውሃ ስለሚቀየር ነው የሚል እምነት አላት (ዮሐ 19:34-35)::

ጥምቀት የዳግም ልደት ምሥጢርን የሚይዝ ሲሆን ጌታ ለቤተክርስቲያን ከሰጣት ትዕዛዛት አንዱ ነው (ዮሐ 28:29-20):: ስኃጢአት ሥርየት፥ ለመንጻትና ለቅድስና አስፈላጊ ነው (1ኛ ጴጥ. 3:21፥ ቲቶ 3:5-6):: ቤተክርስቲያኒቱ በሕፃናት ጥምቀት ታምናለች:: ስለዚህም ሴትን ልጅ በተወለደች በ 80 ቀኗ፥ ወንድን ልጅ ደግሞ በ40 ቀኑ ታጠምቃለች::

ይህ ልማድ ኦሪታዊ መነሻ አለው (ዘሌ. 12:21-24፤ ሉቃ. 2:21-24):: እንዲሁም በመጽሐፈ ኩፋሌ አዳም በተፈጠረ በ40 ቀኑ ሔዋንም በተፈጠረች በ80 ቀንዋ ልጅነት እንደተቀበሉ በመገለጡ ወንዱ በ40 ቀኑ ሴት በ80 ቀንዋ ይጠመቃሉ፤ (ኩፋሌ 4:9-12):: በቂ ውሃ እስካለ ድረስ ጥምቀት በማጥለቅ ይፈጸማል::

እንደ ሠይፈ ሥላሴ አገላለጽ:- «ውሃ መንጽሒ ነው ጥምቀትም ከኃጢአት ያነፃል ውሃ ለሁሉም ነው ጥምቀትም ለሁሉም የታዘዘ ነው፤ ተጠማቂው በሚጠመቅበት ጊዜ 3 ጊዜ በውሃ ውስጥ ብቅ ጥልቅ እንዲል ይደረጋል፤ ጌታችን እንዲሁ ተጠምቋልና (ማቴ 3:16) ሐዋርያትም በዚሁ አይነት ያጠምቁ ነበርና (የሐዋ 8:38)... በምሥጢረ ጥምቀት የውርስ ኃጢአትና ከጥምቀት በፊት የተሠሩ ኃጢአቶች ሁሉ



ይሰረያሉ (ሐዋ. 2:38-39፤ 22:16፤ ቆላ. 2:12-13፤ 1ጴጥ. 3:21)፤ መንፈሳዊ ልደትና ሐዲስ ሕይወት ይገኛሉ፤ (ዮሐ. 3:3-5)፤ ክርስቶስን መምሰል (ገላ. 3:24-26) ቅድስና (ንጽሕና) ኤፌ. 5:25-26)፤ ድኅነት (ማር. 16:16) ይገኛሉ::» በማለት ይገልጻሉ::[90]

### 3.2.1.2. ቁርባን

እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የሚያደርገው በምሥጢረ ቁርባን ነው (ዮሐ. 6:35-57):: በካህኑ ጸሎት ኅብስቱ ተለውጦ አማናዊ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር፥ ወይኑ ተለውጦ አማናዊ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ይሆናል:: ቅዱስ ቁርባን መታሰቢያ አይደለም:: ቅዱስ ቁርባን ልክ በመስቀል ላይ እንደሆነው መስዋዕት ነው::

ቁርባን ከምሥጢራት ሁሉ ታላቅ ምሥጢር ነው:: ይህም ደግሞ ሰው ለእግዚአብሔር ያቀረበው ሳይሆን አግዚአብሕር ለሰው ያቀረበው መሥዋዕት በመሆኑ ቁርባን ይባላል:: አፈጻጸሙም ካህኑ ሥጋውን ዲያቆኑም ደሙን በእርፈ መስቀል ያቀብላል:: በጳጳስ ወይም በካህን ይፈጸማል:: ዲያቆናት የካህኑ ረዳቶች ናቸው:: ለንስሐ የበቁ ብቻ ሥጋወ ደሙን ይቀበላሉ፥ አለያ ግን ዕዳ ይሆንባቸዋል (1ቆሮ. 11:28-29)::

90 ሠይፈ ሥላሴ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖት ... ገጽ 34

እንደ ሠይፈ ሥላሴ አገላለጽ:- «በሚታየው በኅብስቱና በወይኑ የማይታየውን የክርስቶስን ሥጋና ደም እንቀበላለን፤ ሥርየተ ኃጢአትን እናገኛለን (ማቴ. 26፤ 27-28)::»[91] ከክርስቶስ ጋር ኅብረትን እናገኛለን፤ (ዮሐ. 6:56) ከምእመናን ጋርም አንድነት ይኖረናል፤ (1 ቆሮ. 10: 17)፤ በሥጋውና በደሙ የዘለዓለም ሕይወትን እንወርሳለን፤ (ዮሐ. 6:54÷58)::»[92]

### 3.2.2. ትረካዊና በውርስ የተገኙ ሥርዓቶች

ከላይ በትዕዛዛዊ መመሪያ ስር ከተገለጹት ከሁለቱ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምሥጢራት እንደሆኑ የምታምንባቸው አምስቱ:- ምሥጢረ ሜሮን÷ ክህነት ÷ ተክሊል÷ ንስሐ እና ቀንዲል ናቸው::

#### 3.2.2.1. ሜሮን

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተጠማቂው ተጠምቆ እንደወጣ የሚቀባበት ቅዱስ ዘይት ሜሮን በመባል ይታወቃል:: ሜሮን ከዘይት (ወይራ) ከበለስና ከተለዩ ዕፅዋት በጳጳሳት ይፈላል (ይወጣል):: ሜሮን የመቀባት ሥልጣን ለቀሳውስት ተሠጥቷል:: አንድ ሰው በቅዱሱ

---

[91] ሠይፈ ሥላሴ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖት ... ገጽ 39

[92] ዝኒ ከማሁ



ቅባት (በሜሮን) በመቀባት ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ይቀበላል ተብሎ ይታመናል:: ይህም ልክ እንደ እጅ መጫን ሀብተ መንፈስ ቅዱስን የሚያሰጥ ነው ብላ ታምናለች:: ስለዚህ የሜሮን መቀባት ሥርዓት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱ እንደሆነ የምታቀርበው (ኤፌ. 1:13፤ 4:30፤ 2ኛ ቆሮ. 1:21-23፤1ኛ ዮሐ. 1:20-27) ነው::

#### 3.2.2.2. ሢመት (ክህነት)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ክህነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ከፍተኛ የቤተክርስቲያን አገልግሎት እንደሆነ ታምናለች (ኤፌ. 4:11 ሐዋ. 28:20 ማቴ. 28:19-20):: የክህነት አገልግሎት ቃለ እግዚአብሔርን ማስተማር÷ ምሥጢራትን ለመፈጸምና ምእመናንን ለመምራት የሚያስችል መሆኑንም አበክራ ትናገራለች:: ሦስት የስልጣን እርከኖች ማዕረግ እንዳሉት ታምናለች:-

ሀ. ዲቁና:-

ከጋብቻ በፊት ያሉ የሚቀበሉት ሹመት ነው:: ከጋብቻ በኋላ ወይም በድንግልና ለመኖር ከወሰኑ ክህነት ይቀበላሉ:: ለካህኑ ወይም ለጳጳሱ ረዳቶች ናቸው:: ሹመቱ የሚፈጸመው እጅ በመጫን ነው:: ሹመቱን ለመቀበል ክፍያ የለውም:: ሹመት በዘር ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ ሳይሆን በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግ (ቀኖና) አማካኝነት ነው::

ለ. ክህነት (ቅስና):-

ቅስናን የሚቀበሉት ከዲያቆናት መካከል ነው:: ካህናት ከመሾም÷ የክርስትናን ዘይት ከማዘጋጀት÷ አዳዲስ አብያተክርስቲያናትንና አዳዲስ

ታቦታትን ከመባረክ በስተቀር ሌሎች ተግባራትን በሥልጣን ይፈጽማሉ:: በድንግልና ክህነትን የተቀበለ ከሆነ እስከ ጵጵስና መድረስ ይቻላል:: ያገባ ከሆነ ግን በቅስና አገልግሎቱ ይጸናል::

### ሐ. ጳጳስ (ኤጲስ ቆጶስ):-

በድንግልና የተሾመ ካህን ብቻ ለጵጵስና መሾም ይችላል:: ሹመቱም በሌሎች ጳጳሳት በሙሉ የሚሰጥ ነው:: በአስቸኳይ ሹመት መስጠት ካለበት ከሁለት ባላነሱ ጳጳሳት አማካኝነት እጅ በመጫን ሹመት መስጠት ይቻላል:: የጳጳሳት አገልግሎት ቅዱሳት ስርዓቶችን ከመፈጸም ያለፈ አጠቃላይ የእረኝነትና የአመራር ተግባራትን የሚያካትት ነው:: ለጵጵስና የሚሾሙት:- ጤናሞች፥ ለማስተማር እንዲችሉ የተማሩ፥ በሥነ ምግባር የታነጸ ምስክርነት ያላቸው፥ በፆታ ወንድ የሆኑ መሆን ይጠበቅባቸዋል:: የጵጵስና ሹመት በድጋሚ አይፈጸምም::

### 3.2.2.3. ተክሊል

ሥርዓተ-ተክሊል በቤተ ክርስቲያን ጋብቻቸውን ለሚፈጽሙ አባላት ሁለት የቤተ ክርስቲያኒቱ አማኞች ሀብተ መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉ የሚያስችል እንደሆነ ይታመናል:: ጋብቻ የሚፈጸመው በጳጳሱ ወይም በቄሱ አማካኝነት ነው:: ሥርዓተ-ተክሊል በሚፈጸምላቸው ወቅት ሙሽራውና ሙሽሪት ሁለቱም ቅዱስ ቁርባን መውሰድ ይኖርባቸዋል:: በዚህ በምስጢረ ተክሊል የጋብቻ ዓላማ:- 1ኛ. የሰው ዘር እንዳይቋረጥ ዘርዕ ለመተካትና ምድርን ለመሙላት 2ኛ. የባሕርይ ፍትወትን ለማራቅ 3ኛ. ሰው ብቻውን መኖር ስለማይገባውና እርስ በርስ በመረዳዳት



ለመኖር እንደሆነ ታምናለች:: ቤተ ክርስቲያኒቱ ከተጋቢዎች አንዱ ካልሞተ ወይም አመንዝራ ካልሆነ በቀር መፍረስ እንደማይችልም ታምናለች::[93]

### 3.2.2.4. ንስሐ

በቤተክርስቲያኒቱ ትምህርት መሠረት ክርስቲያኖች ለንስሐ አባታቸው ኃጢአታቸውን መናዘዝ ይኖርባቸዋል:: የንስሐ አባት መሆን የሚችሉትም ጳጳሳት ወይም ካህናት ናቸው::ንስሐ አማኙን ተሃድሶ ማግኘት ያስችለዋል:: ስለዚህም በተደጋጋሚ ሊፈጸም ይችላል::

እንደ ሠይፈ ሥላሴ አገላለጽ:- «ተነሳሒው በመምህረ ንስሓው ፊት ቀርቦ ኃጢአቱን በሚገባ ከተናዘዘ በኃጢአቱም ካለቀሰ ስርየተ ኃጢአትን ያገኛል፤ ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቃል፤ የነፍስ ሰላምንና ዕረፍትን ያገኛል፤ በድሎ የነበረው እንዳልበደለ ይሆናል፤ ፍጹም ተሐድሶና ለውጥን ያገኛል::» በመቀጠልም ስለ ቅጣት ሲገልጹ:- «ተነሳሒው የኃጢአቱን ክብደት እንዲያስታውስ ካህኑ:- ለተወሰነ ጊዜ ጾምን እንዲጾም እንዲጸልይ ምጽዋት እንዲሰጥ ከምሥጢራት እንዲከለከል ያዘዋል፤ ይህም በጌታችንና በሐዋርያት ታዝዞአል፤ (ማቴ. 16:19፤ 1ቆሮ. 5:4-5)::» በማለት ያስረዳሉ::[94]

---

[93] ሠይፈ ሥላሴ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖት ... ገጽ 98)

[94] ሠይፈ ሥላሴ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖት ... ገጽ 43-44

### 3.2.2.5. ቀንዲል

ምሥጢረ ቀንዲል ጌታ ለሐዋርያት ድውያንን ዘይት እየቀቡ እንዲፈውሱ በሠጠው ኃይል መሠረት የሚከናወን ሥርዓት ነው:: ቀንዲል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ነው (ማር. 6:13፥ ያዕ. 5:13-15):: ቤተ ክርስቲያኒቱ የቀንዲል ጥቅሙ ለሥጋ ብቻ ሳይሆን ለነፍስም እንደሆነ የሚታመነው ለኃጢአት የሥርየት መንገድ እንደሆነ ባላት ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ነው::

ምሥጢረ ቀንዲል ከፈውስ የጸጋ ስጦታ የተለየ መሆኑን ስታስረዳም:- «ምሥጢረ ቀንዲል በ1ኛ ቆሮ. 12:28 ላይ ከተጠቀሰው ሀብተ ፈውስ የተለየ ነው፤ ማንኛውም ጳጳስ ወይም ቄስ ምሥጢረ ቀንዲልን ለመፈጸም ሥልጣን አለው፤ "ሀብተ ፈውስ" የሚባለው ግን ለተለዩ ሰዎች ነው፤ የተለዩ ከተባለም ለካህን ወይም ካህን ላልሆነ ሊሰጥ ይችላል::»[95]

### 3.2.3. እንማማር

ቤተክርስቲያን በትዕዛዛዊ መንገድ ከጌታ የተቀበለቻቸው ቅዱሳን ሥርዓቶች ጥምቀትና ቅዱስ ቁርባን (የጌታ ራት) ሥርዓቶች መሆናቸው ግልጽ ነው:: ከጥምቀት ሥርዓት ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሜሮን ሥርዓትን ትፈጽማለች:: ይህ የሜሮን ሥርዓት ተጠማቂው ተጠምቆ እንደ ወጣ የሚቀባው ዘይት ተምሳሌተ

[95] ሠይፈ ሥላሴ፥ የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ መሠረተ ሃይማኖት … ገጽ 47



መንፈስ ቅዱስ ሆኖ እጅ መጫንን እንዲያመለክት ሳለው እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃነት የተሰጡት ክፍሎች የሜሮንን ሥርዓት የሚያስረግጡ አይደሉም:: ሀብተ መንፈስ ቅዱስን መቀበል ከጥምቀት ጋር መቆራኘቱንም ማስረገጥ የሚቻል አይመስለኝም::

የአማኞችን ክህነትም በተመለከተ ከሐዋርያት አዕማድ እንደሆነ የተነገረለት ጴጥሮስ በተለያዩ ስፍራዎች ለተበተኑት አማኞች በ1ኛ ጴጥ. 2:9 ሲጽፍላቸው:- «እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃን የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ …» ይላል:: ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው የክህነት አገልግሎት የአማኞች ሁሉ እንጂ ለተወሰኑ ሰዎች የተሠጠ እንዳልሆነ ነው:: ነገር ግን በቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር መንፈስ እንደወደደ ጸጋውን ሲያከፋፍል ለእያንዳንዱ የተለያየ ጸጋን ሠጥቷል:: ከዚህም የተነሳ ላንዳንዶች የመምራትንም ሥጦታ ሰለሰጠ የመሪነት ሥጦታ ያላቸው ሰዎች በመሪነት ስፍራ መቀመጥ ይገባቸዋል::

የቀንዲል ሥርዓትም በያዕ. 5:14 መሠረት በኃጢአት ምክንያት የእግዚአብሔር እጅ የከበደባቸውና የታመሙ አማኞች የቤተክርስቲያን መሪዎች ዘይት ቀብተው እንዲጸልዩላቸው ይገልጻል:: ይህ ደግሞ በተለይ እንደ ከአሕዛብ ወደ ክርስትና የተመለሱና በሐዋ. 19:11-20 ባለው ክፍል የሐዋርያው ጳውሎስን ጨርቅ በመውሰድ የኤፌሶን (ከአሕዛብ ወገን) የሆኑ ሕዝቦች ያሉት በንክኪ የሚያምኑ እንደነበሩ መረዳት ይቻላል:: ስለዚህም በንክኪ የሆነ እምነት ለነበራቸው ሕዝቦች

የሆነ መግቦተ እግዚአብሔር ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቀንዲልን «ህብተ ፈውስ» ስሌላቸው የተሰጠ እንደሆነ ማመኗ ትክክለኛነት ያለው ለመሆኑ ማስረዳት ይቻላል።

## 3.3. ኦርቶዶክሳዊነት ህገር በቀል ወይስ መጤ ግን አውዳዊ?

ከቤተክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ለኢትዮጵያ ክርስትናን ያበሰሩትም ሆኑ መልዕክቱ ኢትዮጵያዊ እንዳልነበሩ ግልጽ ነው። ይህንን ስል የወንጌል መልዕክት የአንድ ህገርም ሆነ ሕዝብ እንዳይደለ፤ ነገር ግን ለዓለም ሕዝብ ሁሉ የማዳን እውነት እንደሆነ ያለኝን ጽኑ እምነት መግለጽ እፈልጋለሁ። ሆኖም የእግዚአብሔር የማዳን እውነት ለምድራችን የመጣበትን መንገድ ስንመለከት በአንድ ሕዝብ ማለትም በአይሁድ ባሕል መገለጡንና የመሲሁም መምጣት ከአይሁድ ዘንድ እንደሆነ እናስተውላለን (ሮሜ 9:6)።

እግዚአብሔር የማዳንን እውነት በአይሁድ ባህል መግለጹ ክርስትናን አይሁዳዊ አያሰኘውም። አሕዛብ ክርስትናን ለመቀበል አስቀድሞ አይሁድ መሆንና የአይሁድን ባህል ባህላቸው ማድረግ እንዳለባቸው አልተሰበከም። ከሃዋርያት አዕማድ የተሰኘው ጴጥሮስ ለአሕዛብ የነበረውን አመለካከት እንዲለወጥ እግዚአብሔር በራዕይ ቢናገረውም «ጌታ ሆይ፥ አይሆንም!» ያለ ስለነበር በብስራተ ወንጌልም ወቅት አሕዛብን ከባህላቸው በማስወጣት አስቀድሞ አይሁድ ቀጥሎም ክርስቲያን መሆን እንደሚችሉ ባለ ጽኑ እምነት መሆኑን መረዳት እንችላለን (ሐዋ. 10 ከገላ. 2 ጋር ይነፃጸር)። ይሁንና የአሕዛብ ሃዋርያ የሆነው ጳውሎስ የወንጌልን የምሥራች ለዓለም ሲያበስር የነበረውን



መረዳት ስንመለከት አክራሪ አይሁድ የሆነውን ሃዋርያው ጴጥሮስንም ፊት ለፊት ተቃውሞታል (ገላ.2፡ 11)። እንዲህ አይነቱን ትምህርት በመቃወም የኅብረትን እንቅፋት ከማስወገድ አንጻር ካልሆነ በስተቀር አሕዛብ ባህላቸውን ሳይለቁ የወንጌልን እውነት በባህላቸው አውዳዊነት እንዲያስተናግዱ አድርገዋቸዋል (ሐዋ. 15)። ስለዚህ የወንጌል እውነት በአይሁድ ባሕል መገለጡ የአይሁድን ባህል እግዚአብሔራዊ እንደማያሰኘው ሁሉ የአሕዛብንም ባህል ሙሉ ለሙሉ ርኩስ አያሰኘ ውም።

ታዲያ ከአይሁድና በአይሁድ ባህል የመጣው መሲህ (ክርስቶስ) ለኢትዮጵያውያን የማዳኑ ወንጌል ሲሰበክ አይሁዳዊ ወንጌል ሳይሆን በኢትዮጵያ አውድ መሆን እንዳለበት ግልጽ ነው። ይህ ደግሞ ከባህል አኳያ ኢትዮጵያዊነት አለን? የሚልን ጥያቄ ከመቀስቀሱም ባሻገር ክርስቲያናዊ ሥነ መለኮት አውዳዊነቱን የጠበቀ ሆኖ በሀገራችን ለመጎልበቱ እንዲሁም አውዳዊ ለማድረግ የተወሰዱ እርምጃዎችን መገምገም የሚያስችል ቅኝት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

### 3.3.1. ኦርቶዶክሳዊነትና የብሉይ ኪዳን እንዲሁም የዕብራውያን ባህል ተጽዕኖ በኢትዮጵያ

ከታሪክ የምንገነዘበው ጥንታዊው የአይሁድ ባህል በኢትዮጵያ ላይ እስከዛሬም ድረስ ግልጽ ሆኖ የሚታይ ታላቅ ተጽዕኖ ማሳደሩን ነው። ይህ ደግሞ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ከኦርየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናትን ጭምሮ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ልዩ እንድትሆን አድርጓታል።

ከላይ ለመዘርዘር እንደሞከርኩት የኢትዮጵያ ባህል በብሉይ ኪዳን የዕብራውያን ባህል ተጽዕኖ ውስጥ በመውደቁ ኢትዮጵያ የአይሁድን ባህል በጥቂቱ ለማስተካከልና ከክርስትና ጋር ለማወራረስ በመሞከር ተቀብላለች:: ከዚህም የተነሳ አይሁዳዊ ባህል ክርስትና ሲለብሰው የሚገባውን ገጽታ እንጸባርቆበታል::

### 3.3.2. ኦርቶዶክሳዊነትና የአረማዊነት ተጽዕኖ በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከአይሁድ ባህል ባሻገር በአረማዊነት ቅሬታም ተጽዕኖ ውስጥ መውደቋን መረዳት ይቻላል:: እንደ ካልቪን ሸንክ አገላለጽ:- «የግሪክና የሴማውያን ባህል ተጽዕኖ እየደበዘዘ ሲመጣም የአረማዊነት ሃይማኖታዊ ልምምዶች እና አይሁዳዊ ወጎች እንደገና ያገረሸበት ወቅት ክርስትናን አገር በቀል ለማድረግ የተሞከረበት ወቅት ነበር::»[97] በመቀጠልም ካልቪን ሸንክ ስለ አረማዊነት ተጽዕኖ ሲገልጹ:- «የአረማውያን አማልክት ሙሉ ለሙሉ አልጠፉም ነበርና መልካምና ርኩስ በመባል ማስተካከያ ተሰጥቶባቸዋል:: ለምሳሌ:- ክርስቲያን ኦሮሞዎች ልጅ የምትሠጥ ሴት አማልክትን (አቴቴ) ከማርያም ጋር በእኩል ደረጃ ይቆጥሯታል:: በተመሳሳይ መንገድ ዛር በሰሜን ኢትዮጵያ የአገው ሕዝቦች ዘንድ 'የሰማይ አምላክ' በመባል የሚታወቀው ሰዎችን የሚቆራኝ መንፈስ ነው:: የዛር መናፍስት የተለያዩ አይነቶች ናቸው:- ወንድ ወይም ሴት እንዲሁም መጥፎ ወይም ጥሩ:: እንደ:- ድንገተኛ÷ እፍዝ አደንግዝ÷ ልባዊ ሃዘን÷ ዳፍንት (አካላዊ ዐይነ ሥውርነትን÷ ሽባነትን ወዘተ) የሚያስከትል ህመም÷ የሚያቀውስ በአጠቃላይ አካላዊ እና የአዕምሮ ህመም የሚያመጡ ናቸው::»[98] ይላሉ::

ከዚህ በተጨማሪ ምንም እንኳን ክርስቲያናዊ እንዲሆኑ ለማድረግ የተሞከሩ ቢገኙበትም ቤተክርስቲያኒቱ ከአረማዊ ልምምድ ያጠመቀቻቸው (ክርስትና ያነሳቻቸው) ሌሎች ልምምዶቿን ስንመለከት:- በጊዮርጊስ÷ ሚካኤል ወይም በገብርኤል ሥዕል የተሰበጠ ከታብ አንገት ላይ የሚታሰርና በደብተራ የሚደገምና በግዕዝ ተጽፎበት በትንሽ ቆዳ ታስሮ በአንገት ላይ የሚንጠለጠል አሰማት (ድግምት)÷ የአንዳንድ ደብተራዎች የሙታን መንፈስ ጠሪነት ወዘተ ይገኙበታል::

### 3.3.3. እንማማር

እግዚአብሔር ሳሰው ልጆች ራሱን የገለጠበትንም ሆነ የአድኅኖት ሥራውን የፈጸመበትን መንገድ ስንመለከት በሰውኛው አገላለጽ ነው:: ስለዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ መልዕክቱ እግዚአብሔር መንፈስ እንደሆነና ማንም አይቶት እንደማያውቅ ሲሆን ሳለ ለሰው ግልጽ በሆነ መንገድ ራሱን ለማስተዋወቅ ግን የሥጋዊ አካል ክፍሎች:- ዐይን÷ እጅ÷ እግር÷ ጆሮ ወዘተ እንዳሉት ሆኖ ተጠቅሷል (ዮሐ. 4:24፤ 1:18 ከኢሳ. 66:1 እና 2 ጋር ይነፃጸር)::

ታዲያ እግዚአብሔር የአንድ ሕዝብ ወይም ብሔር አምላክ ሳይሆን የዓለማት ፈጣሪ እንደ መሆኑ እስራኤልን ሲመርጥ የምድርን አሕዛብ

[97] Calvin Shenk, Missiology: An International Review, p. 261

በእርሷ ለመባረክ እንደሆነም ግልጽ ነው (ዘፍ. 12:1-3):: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር መወለዱም ሆነ የማዳኑ የምሥራች የሆነው ወንጌል በአይሁድ በኩል መምጣቱ ሰዎች ሁሉ መጀመሪያ አይሁድ ሆነው ከዚያ በኋላ ክርስትናን እንዲቀበሉ አልነበረም:: በመላዕክት ልሳን እንኳን ለሰው ዘር መገለጥን ቢሰጥ ኖሮ ሰው ሊረዳው እንደማይችል ያሰበልን አምላክ መገለጥን በቋንቋና በባህል መረጣ አስተናግዶ በዚህ ቋንቋ ባህል ብቻ እኔን ማወቅ ትችላላችሁ የሚል ድንጋጌ የለውም::

ስለዚህም ወንጌል በእያንዳንዱ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ መሰበክ እንዳለበትና ክርስትናም ከየትኛውም ሕዝብ ባህልና ቋንቋ ተጽእኖ ነፃ እንደሆነ ማመንን ይጠይቃል:: ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ወንጌል በባህል ውስጥ ሲሰበክ እንጂ ባህል በወንጌል ውስጥ ሲሰበክ አይገባውም:: ይህም ማለት ደግሞ ክርስትና በሕዝብ ባህል አውዳዊ ሲሆን ሲገባው ባህል ግን በክርስትና እውነት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር አይገባውም::

በሐዋርያዊ ተልእኮ የወንጌል መልዕክተኞች ወደ ተለያዩ የአለማችን ክፍሎች በመጓዝ በሥብከተ ወንጌል ሲሰማሩ የሚጠቀሙባቸውን ሦስት የተለያዩ የአውዳዊነት መመሪያዎች በመቃኘት በምድራችን ከሚስተዋለው ችግር መማር ያሻል:: የወንጌል መልዕክተኞች የሚተገበሯቸው ሦስት አይነት ወንጌልን ዐውዳዊ የማድረግ መመሪያዎች አሉ:-

[98] Ibid, p. 266.



### ሀ. የጥንቱን ተቀበል (Accept the Old)

ይህ «የጥንቱን ተቀበል» የተሰኘው የአውዳዊነት መመሪያ በተለይ በጥንቷ ቤተክርስቲያን የወንጌል መልዕክተኞች ዘንድ ይዘወተር የነበረ ነው:: ወንጌልን ወደ ባዕድ ምድር ይዘው የገቡ የወንጌል መልዕክተኞች በሕዝብ ዘንድ ወንጌል ባዕድ እምነት እንዳይሆን ለማድረግ በሕዝቡ ባህል ውስጥ ለመስበክ ሳይሆን የሕዝቡን ባሕል እንዳለ ክርስትና በማንሳት ክርስቲያናዊ ድጋፍ ለማስጠት መሞከራቸውን እናስተውላለን::

ከዚህም የተነሣ በምድራችን በተለይ በገዳማት በነበሩ የሥነ መስኮት እሳቤዎች ወንጌል አይሁዳዊ ብቻ ሳይሆን አረማዊ እንዲሆንም ተገዷል:: ከላይ የተገለጹት አይሁዳዊና አረማዊ ልምምዶች በወንጌል ላይ ባሳደሩትም ተጽዕኖ፤ ተጽዕኖ ማድረግ የሚገባው የእግዚአብሔር እውነት በተጽዕኖ ውስጥ ወድቆ ባህል ሲቆይ ሃይማኖት ይሆናል እንዲሉ ዛሬ ሃይማኖታችን የተሰኘው በባህል ጥቃት ሥር የዋለው ወንጌል የተሃድሶ ያለ በሚል ጩኸት ውስጥ ይገኛል::

### ለ. የጥንቱን ካድ (Reject the Old)

በዚህ «የጥንቱን ካድ» በተሰኘ የአውዳዊነት ትግበራ መሠረት ደግሞ የጥንት የወንጌል መልዕክተኞች ከፈጸሙት ስህተት እንደምንማረው ከሆነ ወንጌል የአንድ ባህል አጋፋሪ መሆን እንዳለበት ጽኑ እምነትን የሚያንጸባርቅ ነው:: ምንም እንኳን ይህ ዓይነቱ የአውዳዊነት መመሪያ በሰፋት በምድራችን ባይታይም በአንዳንድ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ዘንድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

ለተፈጸመው «የጥንቱን ተቀበል» ለተሰኘው አውዳዊነት አክራሪ ምላሽ ተደርጎ ተንጸባርቋል።

በዚህ «የጥንቱን ካድ» በተሰኘ የአውዳዊነት መመሪያ መሠረት ወንጌል የሕዝብን ባህል መለወጥና የማንኛውም ከወንጌል ውጪ የነበረ ሕዝብ ባህል ሙሉ ለሙሉ አጋንንታዊ ስለሆነ «በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም ክርስቲያናዊ ባህል» መለወጥ ይኖርበታል የሚል ነው። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር በአይሁድ ባህልና ቋንቋ ራሱን መግለጡ የአይሁድን ባህል ሙሉ ለሙሉ ቅዱስ ያሰኘዋልን? የሚልን ጥያቄ ያነሳሳል።

በዚህም መሠረት ሕዝብን ከባህሉ አውጥቶ «ጥቁሩ ፈረንጅ!» የሚያሰኘው በመሆኑ በሕዝቡ ዘንድ ትርጉም የማይሠጥ እንግዳ ትምህርትና እንግዳ ባህል አድርጎት ተቀባይነት ያሳጣዋል። ለዚህ ከግል ሕይወት ተሞክሮዬ በጥቂቱ ያወሳሁትን መድገሙ ጠቃሚ መስሎ ታይቶኛል፡- በ1992 ዓ.ም በአንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሥብከተ ወንጌል አገልግሎት ውስጥ ነበርኩ። ታዲያ በአጥቢያይቱ በየዕሁድ በርካታ ከተለያየ ብሔር እግዚአብሔር አምላክን ለማምለክና ቃለ እግዚአብሔርን ለመስማት የሚሰበሰቡ ሕዝቦች ነበሩ። ከእነርሱም ውስጥ የአንድ ብሔር ተወላጆች የሚበዙበት አካባቢ በመሆኑ በርካታ ሰዎች ለአምልኮ ይሰበሰቡ ነበር።

ሆኖም ግን የዚህ ብሔር ተወላጆች ብዙ ጊዜ በሥብከተ ወንጌል መካከል እንቅልፍ እየወሰዳቸው የሠባኪያኑን ትኩረት መስረቃቸውና በተግሳጽም ባለመወገዱ ችግራቸውን ለማጥናት ሞከርኩ። ለጥናቱ ሠላሳ የሚሆኑ ሰዎችን በነሲብ በመውሰድ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ስሞክር የቋንቋ ችግር መኖሩን ስላስተዋልኩ አስተርጓሚ መጠቀም ግድ



ሆነብኝ። የሚገርመው ከሃያ አምስትና ከሠላሳ አመታት በላይ በአዲስ አበባ የኖሩ አናቶችም እንኳ አማርኛ የግድ እየሰሙ መናገር የማይሆንላቸው ነበሩ። በጥናቱ ማጠቃለያም ላይ ሰዎች በቋንቋቸውና በባህላቸው ወንጌልን መስማትና እግዚአብሔርን ማምለክ እንዳለባቸው ድምዳሜ ላይ በመድረስ በአሁኑ ወቅት በዚያ ብሔር ቋንቋና ባህል ቤተክርስቲያን ተከፍቶ ብዙዎችን በሥብከተ ወንጌል መድረስ ተችሏል።

ከዚህም በመነሳት በምድራችን በኢትዮጵያ እንኳን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ብዛት እንዳላቸው ሁሉ የሕዝቧም ባህል አንድ አለመሆኑን በመገንዘብ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ሕዝብ ውስጥ ለወንጌል እውነት መዳረስ እንደ ድልድይ ሊጠቀምበት ያለውን የባህል ገጽታ ማጥፋትና በእንግዳ ባህል መተካት ወንጌልን ባይተዋር ከማድረጉም ባሻገር የሥርጭት ሀይሉንም ይወስነዋል።

### ሐ. የሄስ አውዳዊነት (Critical Contextualization)

በዚህ «የሄስ አውዳዊነት» በተሰኘው መመሪያ ሥር ክርስትና የሚቀበላቸውም ሆነ የሚክዳቸው የሕዝብ ባህል ክፍሎች እንዳሉ ነው። ስለዚህም ወንጌል ለእያንዳንዱ ሕዝብ ሲሰበክ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያ ውጪ የሆነ ከአጠቃላዩ የእግዚአብሔር እውነት ጋር የሚቃረን እምነትንና ልምምድ ሲካድ፤ ለክርስቲያናዊ ሕይወት ጎጂ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ በባሕል ቀይር ምክንያት ለወንጌል አንቅፋት አለማኖርን ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ስለዚህም ነው በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ልትከዳቸው በመምከር ላይ ያለችውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌላቸው አይሁዳዊም ሆኑ አረማዊ ልምምዶች በማስወገድ እና ለክርስትና ሕይወት ጠቃሚ የሆኑ የእግዚአብሔር እውነት ለኢትዮጵያውያን የተገለጠባቸውን የባህል ገጽታዎች ማጎልበትን ልትገፋበት ይገባል። ከዚህም የተነሣ የትኞቹ የዕብራዊያንና የአረማውያን ባህል ገጽታዎች በነብያትና በሃዋርያት ከተሰበከውና እግዚአብሔር በዘመኑ መጨረሻ በገዛ ልጁ ለእኛ ከተረከልን የክርስትና እውነት ጋር ተቃርኖ ስላላቸው የወንጌልን እውነት እንዳያዳፍኑ ሊካዱ የሚገባቸው የባዕድ ባህል ገጽታዎች እንደሆኑ በመገምገም አውዳዊት ሊሄስ እንደሚገባው ካለው የሥብከተ ወንጌል መመሪያ ጋር የሚስማማ ትግበራት ለአንባቢዎቼ መተው እፈልጋለሁ።



## ማጠቃለያ

የቤተክርስቲያን አንድነት በፖለቲካ ተጽእኖ እንዲሁም ነገሥታት የራሳቸውን ዝናና ክብር ለማስጠበቅ ከነበራቸው ህልም የተነሣ አደጋ ላይ መውደቁን ታሪክ በተጨባጭ ማስረጃ ያመለክተናል። በመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን ወቅት የነበረው የፖለቲካ እንቅስቃሴ ዛሬም ቢሆን ቤተክርስቲያንን መጠቀሚያ የማድረግ ሒደቱ አልተገታም። ይሁንና ለውጡ የሚስተዋለው ቤተክርስቲያን ከመንግሥት ተለይታ በራሷ ከተጽእኖ ውጪ ለመንቀሳቀስና ነፃነቷን መጠቀም የሚያስችላት ደረጃ ላይ በመድረሷ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ዘመናችን የእውቀት ዘመን በመሆኑ የሰው ልጅ ከታሪክ ለመማር እንጂ «በጠላት ይቀባል ጥላት!» አባባል ተፈጻሚነት አንዳንድ ያልተማሩ መሪዎቿ ለሕዝባቸው በሚያስተጋቡት ከፋፋይ አሉባልታ የማይደናገርበት ወቅት በመሆኑ ነው።

ስለዚህም ቤተክርስቲያን በየትኛውም ዘመን ፍጹም ሆና እንደማታውቅ በማስተዋል በመሠረታዊ ነጥቦች ላይ ከቃለ እግዚአብሔር ያፈነገጡ ትምህርቶችንና ልምምዶችን በመማማር ለማረም የተከፈተ ልብ ያሻታል።

የቤተክርስቲያን አባቶች ሊረዱት የሚገባው መሠረታዊ ነገር ከታሪክ በመማር ሀገራችን ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ያለችበት ሁኔታ በብዙ አቅጣጫ አስተርእዮተ እግዚአብሔር በሌላቸው እንዲሁም ለኋላ ቀርነታችን መንስኤ በሆኑ ትምህርቶችና ልምምዶች የተተበተበች መሆኗ ነው። እንግዲህ መንፈሳዊውን ከሥጋዊው በሚነጣጥልና በሚያራርቅ

እሳቤ ካልተመሰከትነው በስተቀር የሀገራችን ሁስንተና በእውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ብቻ መዳሰበ ይኖርበታል። የምዕራቡ ዓለም ዕድገት! የእኛ ግን ፊተኞች ኋለኞች መሆን ምሥጢሩ ከቃለ እግዚአብሔር ያፈነገጡ የታሪክ ጠባሳዎች የሁሰንተናዊ ዕድገት ማነቆነታቸው ነው። የሚገርመው ደግሞ:- «የተሰያየ ሃይማኖት ያላቸው ሰዎች ተሥማምተውና ተቻችለው የሚኖሩባት ሀገር!» መባሏ ዕድገትን ማበመዝገብ የሚያስችል አንድነት አለመሆኑን ታሪካችን ገሃድ ያደረገው መሆኑ ነው።

ስለዚህም የኢትዮጵያ እንቆቅልሽ ያለው በታሪክ በመኩራራት እንጂ ከታሪክ በመማር ላይ ባለመሆኑና ዘመናችንን በሙሉ በአንዳንድ አባቶች ውድቀት ስንመጻደቅና እግዚአብሔርን ያገለገሉ መስኋቸው ያሳደዱትንም በጻድቃን ተርታ መድቦ በእነርሱ ስም በተሰየሙ ቀናት የሥራ ፈትነት ባህልን ያጎለበቱትን አባቶች ዱካ መከተል በመሆኑ እርስ በርስ ለመማማር ዕድሉን አጨልመነው ኖረናል። እንግዲህ ከታሪክ የመማርን ባህል አዳብረን አንዳችን ከሌላችን ተምረን ላለፉ ዘመኖች ስህተቶቻችን በምሕረት መንፈስ ተነሥተን ለሁለንተናዊ ዕድገት መጎልበት የየበኩላችንን አስተዋጽኦ ልናበረክት ይገባል።



## ዋቤ መጻሕፍት

ሠይፈ ሥላሴ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መሠረተ ሃይማኖት እና የካህናት ተልዕኮ፥ አዲስ አበባ፡ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፥ ሰኔ 21/ 1982 ዓ/ም

ጎርጎርዮስ (አባ) ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፥ አዲስ አበባ:- ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፥ 1994 ዓ/ም

ጠቅላይ ቤተክህነት፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን እምነት፥ ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት ፥ አዲስ አበባ:- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ሐምሌ 1988 ዓ/ም

Bahru Zewde: *A History of Modern Ethiopia*: 1855-1974, Addis Ababa, University Press, 1991

Beyene Dollicho (Dr.) *Introductory Geography of Ethiopia*, Addis Ababa, AAU Department of Geography

Bruce, F.F, *The Canon of Scripture*, Illiinois 60515, InterVarsity Press, 1988.

Getechew Haile, Aasulv Lande & Samuel Rubenson, *The Missionary Factor in Ethiopia*

Jones, A.H.M and Elizabeth Monroe, *A History of Ethiopia*, Oxford University Press, 1935

Sergaw Hable Sellassie, Ancient and Medivial Ethiopian History to 1270, Addis Ababa: Haile Selassie I Univerdity, 1972

Sergaw Hable Sellassie and Taddesse Tamrat. *The Church of Ethiopia: A Panorama of History and Spiritual Life.* Addis Ababa: United Printers, 1970.

Shenk, Calvin. *Ethiopian Religion*, Nazreth: Bible Academy. 1970.

Shenk, Calvin, *The Development of the Ethiopian Orthodox Church and Its Relation with Ethiopian Government from 1930-1970* (Un published PhD. Dissertation), 1973.

Shenk, Calvin, Missiology: An International Review, Vol.XVI, No. 3. July 1988

Tadesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia 1270-1527*, Oxford 1972

Tesfazghi Uqbit, *Current Christological Positions of E.O.C Theologians*. Rome: Pontifica Institutum Studiorum Orientatium, 1973.

ቃለ መጠይቅ፡-

አፈወርቅ (መላከ ገነት)፥ ኅዳር 12/ 1993 ዓ/ም፥ መኖሪያ ቤታቸው

ጸጋዬ ደምሴ፥ ኅዳር 7/ 1993 ዓ/ም፥ ሙራ መጽሔት ቢሮ